# የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

## ኢሰመጉ

## 38ኛ መደበኛ መግለጫ

# የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በኢትዮጵያ

የምዝገባ ቁጥር 1146

መስከረም 2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢሰመጉ - EHRCO


**ዋና ጽ/ቤት፡ አዲስአበባ**

አ.አ ስታዲየም አጠገብ፣ላሊበላ ሬስቶራንት ጎን፣ ሣኅለ ሥላሴ ሕንፃ 8ኛ ፎቅ፣ቢሮ ቁጥር 19

ስልክ: (+251) 011 551-7704

ፋክስ: (+251) 011 551-7704

ኢ-ሜይል: info1hrco@gmail.com info@ehrco.org

ድረገጽ: www.ehrco.org

ፌስቡክ፡ https://www.facebook.com/ehrco1/

ትዊተር፡ https://www.twitter.com/ehrcoethio

ቴሌግራም፡ https://t.me/ehrco

የፖስታ ሳጥን ቁጥር 2432

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

**የሰብዓዊ መብቶች ክትትል እና ምርመራ መምሪያ**

ስልክ: (+251) 011 558-2387

ኢሜይል: info1hrco@gmail.com / info@ehrco.org

**ቀጠና / ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች**

| | |
|---|---|
| ደቡብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡- | ሐዋሳ - ስ.ቁ (+251) 046 220-4500፣ፖ.ሳ.ቁ 360 |
| ሰሜን ኢትዮጵያ ቀጠና፡- | ባሕርዳር- ስ.ቁ (+251) 058 220-0240፣ፖ.ሳ.ቁ 1115 |
| ምዕራብ ኢትዮጵያ ቀጠና፡- | ነቀምቴ - ስ.ቁ (+251) 057 660-2664፣ፖ.ሳ.ቁ 463 |
| ምሥራቅ ኢትዮጵያ ቀጠና፡- | ድሬደዋ - ስ.ቁ (+251) 025 411 6845፣ፖ.ሳ.ቁ 2596 |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ቀጠና፡- | አዲስአበባስ.ቁ (+251) 011 551-7704፣ፖ.ሳ.ቁ2432 |
| መቀሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፡- | መቀሌ - ስ.ቁ. (+251) 034 241-3696 |
| ጎንድር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፡- | ጎንደር - ስ.ቁ. (+251) |
| ጋምቤላ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፡- | ጋምቤላ - ስ.ቁ. (+251) |

ማውጫ

1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ ........ 5

2. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ........ 6

3. የመደበኛ መግለጫው ዓላማ፣ የምርመራ ሂደትና ዘዴዎች ........ 8

3.1. የመደበኛ መግለጫው ዋና ዓላማ........ 8

3.2. በምርመራው ሂደት ተጥሰው የተገኙና በመደበኛ መግለጫው የተካተቱ የሕግ ማዕቀፎች........ 8

3.3. የመረጃ ምንጮችና የምርመራ ዘዴዎች........ 8

3.4. የምርመራ ሥራው ውሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች........ 9

ክፍል አንድ........ 10

4. በሐገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ውስጥ የተፈፀሙ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች........ 10

4.1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማና በተለያዩ ቀበሌዎች በብሔር ላይ ያነጣጠረ ጥቃትና የተፈፀሙ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ........ 10

4.1.1. በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ-ወጥ ግድያ) ........ 12

4.1.2. የአካል ጉዳት (ማቁሰል)........ 20

4.1.3. ከቤት ንብረት መፈናቀል ........ 21

4.2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ሰሜን ሸዋ ዞንና የኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ........ 23

4.2.1. የጥቃቱ መነሻ ታሪክ........ 23

4.2.2. በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ-ወጥ ግድያ) ........ 24

4.2.3. አካል ጉዳት........ 28

4.2.4. ማፈናቀል ........ 32

4.2.5. ጉዳዩ አሁን የሚገኝበት ሁኔታ........ 35

4.3. በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ማንዱራ ወረዳ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ........ 35

4.4. በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ሲዳማ ዞን የተለያዩ አካባቢዎች ውስጥ የተፈጸሙ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች........ 36

4.4.1. መግቢያ........ 37

4.4.2. የችግሩ የኋላ ታሪክ ........ 37

4.4.3. በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ)........ 38

4.4.4. የአካል ጉዳት (ማቁሰል)........ 43

4.4.5. የንብረት ውድመት ........ 46

4.4.6. በኃይማኖት ተቋማት ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች........ 46

4.5. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ ውስጥ መኖሪያ ቤታቸው የፈረሰባቸው ዜጎች ጉዳይ ........ 49

4.6. በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ሐረር ከተማ ጥር 10 እና 11 ቀን 2012 ዓ.ም የደረሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ........ 50

4.7. ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ........ 52

ክፍል ሁለት ........ 58

5. ማሳሰቢያ ........ 58

6. ማጠቃለያ ........ 60

# 1. የኢትዮጵያ አስተዳደር ክልል እና ዞን ካርታ



## 2. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በበጎ አድራጎትና ማኅበራት አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት አገር በቀል ድርጅት ሆኖ በምዝገባ ቁጥር 1146 ከ02/11/11 ዓ.ም ጀምሮ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ኤጀንሲ ዳግም ተመዝግቦ በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው። ኢሰመጉ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ሲሆን፣ ዓላማውም በኢትዮጵያ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው።

ኢሰመጉ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የኃይማኖት ተቋም፣ የብሔረሰብ ቡድን፣ ማህበራዊ መደብ ወዘተ የማይወግን፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋም ነው። ኢሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው። ኢሰመጉ ላለፉት 28 ዓመታት በቆመላቸው ዐበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ ሁለንተናዊ፣ ሐገራዊና ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ በነደፋቸው በርካታ የመርሐ -ግብር ተግባራት አማካኝነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ የሕግ የበላይነትና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲኖር የበኩሉን አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ ይገኛል።

ዓበይት ዓላማዎቹንና ተልዕኮውን ለማሳካት ኢሰመጉ ፈርጀ ብዙ የሆኑ የመርሐ ግብር ተግባራትን ያከናውናል። ከእነዚህም መካከል አንዱ በየደረጃው ለሚገኙ የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ለሕዝብ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና መስጠት ነው። የመንግሥት አካላት በዋነኛነት የግዴታዎች ተሸካሚ፣ ሕዝብም በዋነኛነት የመብቶች ባለቤት እንደመሆናቸው መጠን፣ የመንግሥት አካላትም ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታቸውን በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዘው እንዲወጡ፣ ሕዝብም እንዲሁ በዕውቀት፣ በችሎታና በጽኑ እምነት ላይ ተመርኩዞ መብቱን እንዲያስከብር ኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል። በተጨማሪም ኢሰመጉ በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን ይሠራል፤ ውጤቶቹን በተለያዩ የምክክር መድረኮችና በልዩ ልዩ የመገናኛ መንገዶች ያሠራጫል፤ የአድቮኬሲ ሥራዎችንም ያከናውናል።

የኢሰመጉ መለያውና ግንባር ቀደም ተግባሩ በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶችን አያያዝና ሁኔታ መከታተል፣ የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ማጣራትና በማስረጃ የተደገፉ መግለጫዎችን ማውጣት ነው። ኢሰመጉ በሚያወጣቸው መግለጫዎች ሁሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ፍትሕና ካሣ እንዲያገኙ፣ የጥሰት ፈጻሚዎች በሕግ እንዲጠየቁና ወንጀል ሠርቶ በነጻ መሄድ እንዲያበቃ፣ ከእያንዳንዱ ክስተት ትምህርት ተወስዶ ለወደፊቱ ጥንቃቄና ተገቢው የፖሊሲና የአፈጻጸም እርማት እንዲደረግ ሲጮህና ሲጠይቅ ቆይቷል፣ አሁንም በመጠየቅ ላይ ነው፤ ለወደፊትም በዚሁ ይቀጥላል። ከኢሰመጉ የሰብዓዊ መብቶች ክትትል ተግባራት መካከል፣ የሕግ ታራሚዎችን መጎብኘትና ሰብዓዊ መብቶቻቸው መጠበቃቸውን መከታተል፣ የፍርድ ቤቶችን ሂደት ፍትሀዊነት መከታተል እንዲሁም በመንግሥት የወጡና የሚወጡ ሕጎችን ይዘትና አፈጻጸማቸውን ከሰብዓዊ መብቶች አንጻር መመርመር ይገኙበታል። ከእነዚህ በተጓዳኝ ኢሰመጉ በተለይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሰለባ ለሆኑ ዜጎች የተለያየ ደረጃና መልክ ያለው የሕግ ድጋፍ ይሰጣል።

በእስካሁኑ ቆይታው ኢሰመጉ 38 መደበኛ መግለጫዎችና 146 ልዩ መግለጫዎችን በተጨማሪም በተለያዩ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በርካታ ጋዜጣዊ መግለጫዎችን ይፋ አድርጓል። ኢሰመጉ አሁን በሚገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆኖም ቢሆን፣ ሁኔታና ዐቅም በፈቀደለት መጠን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፣ የሕግ የበላይነትና የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ካለው የጸና ዓላማ አኳያ በመሥራት ላይ ይገኛል።

# 3. የመደበኛ መግለጫው ዓላማ፣ የምርመራ ሂደትና ዘዴዎች

## 3.1. የመደበኛ መግለጫው ዋና ዓላማ

የዚህ መደበኛ መግለጫ ዐቢይ ዓላማ ከ2010 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም መጨረሻ በኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን በበቂ ማስረጃ አስደግፎ በማቅረብ በሚመለከታቸው የክልልና የፌደራል መንግሥት አካላት መፍትሄ እንዲሰጣቸው፣ ጥሰቶች እንዲቆሙና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ የመከላከል እርምጃ እንዲወሰድ ለማሳሰብ፣ ጉዳት የደረሰባቸው ሰዎች ተገቢውን የሞራል እና የገንዘብ ካሳ እንዲሰጣቸውና ድርጊቱን ያቀዱ፣ የፈጸሙና ያስፈጸሙ አካላት በሕግ እንዲጠየቁ፣ ጥሰት ፈጽሞ ሳይጠየቁ የመቅረት ልማድ (Culuture of Impunity) እንዲቆምና ተመሳሳይ የመብት ጥሰቶች በድጋሚ የማይፈጸሙበት የተቋማት ግንባታ፣ እንዲሁም የፖሊሲ፣ የሕግና የአሰራር ማስተካከያዎችና እርማቶች ከወዲሁ በተጨባጭ እንዲደረጉ መጠየቅና መጎትጎት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) የዚህን መደበኛ መግለጫ ይዘትና ዓላማ በተዛረረ መልኩ፣ ከሕግና ከመልካም አስተሳሰብ ውጪ ማንም እንዲጠቀምበት አይፈቅድም፡፡ ይህንንም መግለጫ ሰላምን ለማደፍረስና ከሕግ አግባብ ውጪ ሌሎች ሲጠቀሙበት ቢገኝ ኢሰመጉ ኃላፊነትን አይወስድም፡፡

## 3.2. በምርመራው ሂደት ተጥሰው የተገኙና በመደበኛ መግለጫው የተካተቱ የሕግ ማዕቀፎች

በዚህ መደበኛ መግለጫ ውስጥ ይፋ የተደረጉ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ዓይነትና ዘርፍ ለመለየት፣ ለመረዳትና ለማሳየት በዋና መሠረትነት የሚያገለግሉት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግስት፣ የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውና ግዴታም የገባችባቸው ሁሉ-አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ፣ የዓለም-አቀፍ የሲቪል እና ፖለቲካዎች የቃል-ኪዳን ስምምነት፣ የዓለም አቀፍ የኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ መብቶች የቃል-ኪዳን ስምምነት እና የተለያዩ የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫዎች ናቸው፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በየዘርፋቸው በተገለጹበት ቦታ ሁሉ እነዚህ የሕግ ማዕቀፎች በመነሻነትና በማመሳከሪያነት ተጠቅሰዋል፡፡

## 3.3. የመረጃ ምንጮችና የምርመራ ዘዴዎች

ኢሰመጉ በምርመራው ከተጠቀመባቸው የመረጃ ምንጮች መካከል ዋነኞቹ የሰብዓዊ መብት ጥሰቱ ሰለባዎች፣ የተጎጂ ቤተሰቦች፣ የዓይን እማኞችና ምስክሮች እንዲሁም የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶቹ በተፈጸሙባቸው አካባቢዎች ነዋሪዎች የሆኑ ዜጎች ናቸው፡፡ ዋነኞቹ የምርመራ ዘዴዎች የሠነዶች ማሰባሰብና ፍተሻ፣ በፎቶግራፍ የተደገፉ የመስክ ጉብኝቶች ግኝቶች (ጥሰት በተፈጸመባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት)፣ ከተጎጂዎችና ከምስክሮች ጋር በቦታዎቹ ላይ የተደረጉ ቃለ መጠይቆች፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ዜጎችና አካላት ጋር የተደረጉ የቡድን ውይይቶች ሲሆኑ፤ የተገኘውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥም ከጤና ተቋማት፣ ከአስተዳደርና ከፖሊስ አካላት ተጨማሪ ማስረጃ ተሰብስቧል፡፡ ኢሰመጉ በዚህ ምርመራው የተለያዩ ማስረጃዎችን በማሰባበሰብና ጉዳቱንም በአካባቢዎቹ ተገኝቶ በመመልከት ይህንን 38ኛ መደበኛ ሪፖርት አዘጋጅቷል፡፡ ኢሰመጉ የተለያዩ ማስረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩት ሰዎችና መንግሥታዊ ተቋማት ምስጋናውን በዚህ አጋጣሚ ያቀርባል፡፡

### 3.4. የምርመራ ሥራው ውሱንነትና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

38ኛው መደበኛ መግለጫ በሚዘጋጅበት ወቅት ሐገራችን ኢትዮጵያ በተለየ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበረችበት ጊዜ እንደመሆኑ መግለጫውን በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ውስንነቶች እና ተግዳሮቶች አጋጥመዋል። በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ በብዙ የሐገሪቱ አካባቢዎች ይከሰቱ በነበሩ ግጭቶችና አለመረጋጋቶች የተነሳ ይፈጠሩ የነበሩት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ስፋት፣ ጥሰቶቹን ለማጣራት ከመንግሥትና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር መረጃዎችን ለማግኘት የነበሩት አዳጋች ሁኔታዎች፣ ጥሰቶቹ ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለማረጋጋጥ ከተጎጂዎች እና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የነበሩ የግንኙነት መንገዶች በልዩ ልዩ ምክንያቶች መቋረጣቸው እና የራሱ የኢሰመጉ ተቋማዊ ውስንነቶች መግለጫው ጥሰቶቹ በተፈጸሙበት አፋጣኝ ጊዜ ውስጥ እንዳይወጣ አድርጎታል። ከዚህም ባለፈ፤ ይህን መግለጫ በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ ኢሰመጉ የሚከተሉት ዋና ዋና ውስንነቶች እና ተግዳሮቶች አጋጥመውታል፦

- ✓ ኢሰመጉ ያለበት ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ፣ የሰው ኃይልና የምርመራ ቁሳቁስ እጥረት፤
- ✓ በአጠቃላይ በሐገሪቱ የነበረው ፖለቲካዊ ኹኔታ በውጥረት የተሞላ መሆኑና በኢሰመጉ የምርመራ ሠራተኞች ላይ የመንግሥት የደኅንነትና የጸጥታ ኃይሎች ከፍተኛ ክትትል እና ጫና ማድረጋቸው፤
- ✓ በምርመራ ሥራው በተሸፈኑት አካባቢዎች ይፈፀም የነበረው መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የደረሰው ሰብዓዊ ቀውስ ከኢሰመጉ የማጣራት አቅም በላይ መብዛቱ፤ እንዲሁም
- ✓ ከፖሊስና ከሆስፒታሎች የተገኙ አንዳንድ ማስረጃዎች በደፈናው የቀረቡ በመሆናቸው ምክንያት ሟቾችን በተመለከተ ዝርዝር ትንታኔ ለማቅረብ አልተቻለም።

## ክፍል አንድ

# 4. በሐገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ውስጥ የተፈፀሙ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

ሰንጠረዥ 1፡ በዚህ ምርመራ የተሸፈኑ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች

| ተ.ቁ | ክልል | ከተማ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|
| 1. | የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | ቡራዩ ከተማ አስተዳደር | ለኩ ከታ |
| | | | መልካ ገፈርሳ |
| | | | ገፈርሳ ጉጂ |
| | | | ገፈርሳ ኖኖ |
| | | | ቡራዩ ከታ |
| 2. | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር | ኮልፌ፣ አዲስ ከተማ፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ ቂርቆስ እና አራዳ ክፍለ ከተሞች | ከፖሊስ ባገኘነው ማስረጃ በእነዚህ ክ/ከተሞች የተለየ ወረዳና ቀበሌ አልተገለጸም |
| 3. | የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | ሰሜን ሸዋ ኤፍራታ ግድም ወረዳ | አጣዬ፣ ማጀቴ፣ ቆሪሜዳ፣ ካራቆሬ |
| 4. | የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት | የኦሮሞ ብሔረሰብአስተዳደር ልዩ ዞን | ከሚሴ፣ ጆሌ ጡሙጋ፣ አርጡማ ፉርሲ፣ ጨፋ ሮቢት |

## 4.1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ቡራዩ ከተማና በተለያዩ ቀበሌዎች በብሔር ላይ ያነጣጠረ ጥቃትና የተፈፀሙ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

**መግቢያ፡**

ከ2007 ዓ.ም መባቻ ጀምሮ በሐገሪቱ የተለያዩ አከባቢዎች በታየው ሕዝባዊ እምቢተኝነት ገፋፊነት በገዢው ፓርቲ መካከል በተደረገ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግር በመጋቢት ወር 2010 ዓ.ም አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር መሰየሙ ይታወቃል፡፡ ከዚህ ኹነት በኂላ ትጥቅ ትግል ሲያደርጉ የነበሩ ፖለቲካ ፓርቲዎችን ወደ ሐገር ውስጥ እንዲገቡ ማድረግን ጨምሮ በሀገሪቱ ዘርፈ ብዙ ፖለቲካዊ ለውጦች መደረጋቸው ይታወሳል፡፡ ነባራዊ ፖለቲካዊ ስርዓቱ በዚህ አውድ ውስጥ እያለ በተለይም

አርበኞች ግንቦት 7 እና የኦሮሞ ነጻነት ግንባር አባላትና አመራሮች ወደ ሐገር ውስጥ መግባታቸውን ተከትሎ በተፈጠረ ውጥረት በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ቀውስ ተፈጥሯል፡፡

ከጳጉሜ 3 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ በቡራዩ ከተማና በተለያዩ ቀበሌዎች ብሔር ተኮር ጥቃት በመፈጸሙ የበርካታ ዜጎች ሕይወት ጠፍቷል፣ የአካል ጉዳት ደርሷል፣ ንብረት ተዘርፏል፣ ከጥቃቱ የተረፉትም አካባቢውን ጥለው ለመሰደድ ተገድደዋል፡፡ በተጠቀሰው ጊዜ በሥፍራው መጠነ ሰፊ ብሔር ተኮር ጥቃት ከመፈጸሙ በፊት የፖለቲካ ወትዋቾችና የአካባቢው የመንግሥት ባለ ሥልጣናት ‹‹ማንም ሰው በአገሩ ክልል ውስጥ በነጻ የመዘዋወርና የመኖር መብት አለው›› ከሚለው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌና በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 32 ንዑሥ አንቀጽ 1 ስር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ በሐገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሐገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት ነጻነት እንዳለው ከተደነገገው በተፃራሪ የአካባቢው ተወላጅ ያልሆኑ ነዋሪዎችን ‹‹ከመሬታችን ልቀቁ›› እያሉ ጫና ያሳድሩባቸው እንደነበር የብሔር ተኮር ጥቃቱ ሰለባ የሆኑ ተጎጂዎች ለኢሰመጉ ገልጸዋል፡፡

ጥቃቱ በተፈጸመበት ሰሞንም ወደ አገር ቤት የገቡ የኦሮሚያ ነጻ አውጪ ግንባር አመራር አባላትን ለመቀበል ከተለያዩ ሥፍራዎች በመነሣት በቡራዩ በኩል ወደ አዲስ አበባ የመጡ ‹‹ቄሮ›› በተባለ ሥያሜ በሚጠራ ቡድን የሚንቀሳቀሱ ወጣቶች ‹‹ዶርዜ ይውጣ!›› የሚል መፈክር እያሰሙ፣ እየጨፈሩ ብሔር የለየ ጥቃት ማድረስ መጀመራቸውን ኢሰመጉ ባደረገው ምርመራ አረጋግጧል፡፡ ብሔርን የለየ ጥቃት ሲፈጸም በአካባቢው የነበሩ የፖሊስ አባላት ‹‹መንገድ ስለሌለ ወደ መንደር ገብተን ድርጊቱን ለማስቆም አልቻልንም›› የሚል ምላሽ በመስጠት የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ የመከላከል ኃላፊነታቸውን ሳይወጡ ቀርተዋል፡፡

ከጳጉሜ 3 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም ወር 2011 ዓ.ም የመጀመሪያ ሳምንት መጨረሻ ድረስ በኦሮሚያ ክልል በቡራዩ ከተማ በስፋት የተፈፀሙ ብሔርን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶች፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተሞች ማለትም በአዲስ ከተማ፣ በኮልፌ ክፍለ ከተማ፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ፣ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ በአራዳ ክፍለ ከተማ በተፈጠሩ ግጭቶችና በቡራዩ የተፈጸመውን ብሔር ተኮር ጥቃት ለመቃወም ሰልፍ በወጡ ሰላማዊ ዜጎች ላይ የመንግሥት የጸጥታ አካላት ያልተመጣጠነ ኃይል በመጠቀም በወሰዱት እርምጃ የሞትና የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ ችግሩ በተፈጠረበት አከባቢ በመንቀሳቀስና ተፈናቃዮች በተጠለሉባቸው አካባቢዎች በመዘዋወር ችግሩን ተመልክቷል፣ የተጎጂዎችንና የተጎጂ ቤተሰቦችን ቃል ተቀብሏል፡፡ በሌላ በኩል የሚመለከታቸውን የተለያዩ የመንግስት መ/ቤቶችም በችግሩ ዙሪያ እንዲገልጹልን በደብዳቤ በመጠየቅ ምላሽ አግኝቷል፡፡ የቡራዩ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በደብዳቤ ቁጥር Q/p/m/b/671/2011 በ30/02/2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በተፈጠረው ሁከትና ብጥብጥ ሳቢያ የደረሱ ጉዳቶችን በተመለከተ በሰጠን ማብራሪያ የተፈናቀሉ አባወራዎች ብዛት 1221፣ የቤተሰብ ብዛት በድምሩ 4506 መሆናቸውን ገልጿል፡፡

በደብደባ የተጎዱ ሰዎችና ወደ ህክምና የተላኩ ሰዎች ብዛት ወንድ 278፣ ሴት 37 በድምሩ 315 እንደሆነ ከነዚህም ውስጥ ለተሻለ ህክምና ‹‹ሪፈር›› የተባሉ ሰዎች ብዛት ወንድ 114፣ ሴት 6 በድምሩ 120 ናቸው፡፡ ታክመው ወደ ቤታቸው የተመለሱ ሰዎች ብዛት ወንድ 164፣ ሴት 31፣ ድምር 195

ሲሆን ከመስከረም 3 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ መስከረም 5 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ በቡራዩ ከተማ ውስጥ በተፈጠረ ሁከትና ብጥብጥ ምክንያት 36 ሰዎች የሞቱ መሆናቸውን በደብዳቤ ለኢሰመጉ አሳውቋል፡፡

የቡራዩ ጤና ጣቢያ በቁጥር BHC/2506/11 በ24/1/11 ዓ.ም ለኢሰመጉ በላከው ደብዳቤ እንዳስታወቀን ከጤና ጣቢያው ወደ ሆስፒታል ‹‹ሪፈር›› የሆኑት ሰዎች ብዛት ወንድ 80፣ ሴት 6 በድምሩ 86 ሰዎች መሆናቸውን፣ በቡራዩ ጤና ጣቢያ ህክምና ያገኙ ወንድ 123፣ ሴት 22 በድምሩ 145 ሰዎች ሲሆኑ ሞተው ወደ ቡራዩ ጤና ጣቢያ የገቡት ሰዎች ብዛት ወንድ 11 መሆናቸውን ለኢሰመጉ አሳውቋል፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ አቤት ሆስፒታል በደብዳቤ ቁጥር አቤት/ሆ/02/545 በ29/01/11ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ከመስከረም 2 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ ተኝተው የታከሙና ታክመው የተመለሱ 306 ተጎጂዎችን የስም ዝርዝር ከ10 ገጽ  አባሪ ጋር በማያያዝ  ለኢሰመጉ አሳውቋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ኮሚሽን በደብዳቤ ቁጥር አ/አ/ፖ/ወ/መ/ቁ/01/5721/11 በ06/02/2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለኢሰመጉ እንዳስታወቀው ከመስከረም 3 ቀን 2011 ዓ.ም እስከ መስከረም 8 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ በአዲስ ከተማ ክ/ከተማ 4፣ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ 14፣ በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ 4፣ በቂርቆስ ክ/ከተማ 5፣ በአራዳ ክ/ከተማ 1 ሰው በድምሩ 28 ሰዎች ሞተዋል፡፡

ይህ ሪፖርት በሚጠናቀርበት ወቅት በዚህ ድርጊት እጃቸው አለበት ተብሎ የተጠረጠሩ ግለሰቦች ተይዘው ጉዳያቸው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እየታየ የነበረ ቢሆንም፤ ከፊሉ ፍ/ቤቱ በሰጠው ብይን፣ በርከት ያሉት ተጠርጣሪዎች ደግሞ የኮሮና ቫይረስ በሐገራችን መከሰትን ተክትሎ መንግሥት በሰጠው ምህረት የተለቀቁ መሆናቸውን ኢሰመጉ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

ቀደም ሲል ለመጥቀስ እንደተሞከረው በወቅቱ ተከስቶ በነበረው ጉነት የተነሳ በሐገሪቱ ሕገ መንግሥት በግልጽ እውቅና የተሰጣቸው ብሎም፤ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችም መከበር፣ ማስከበር እና መጠበቅ ይገባቸዋል የሚሏቸው ሰብዓዊ መብቶች በግልጽ ተጥሰዋል፡፡ ከእዚህ በመነሳት በወቅቱ የተጣሱት ሰብዓዊ መብቶች እደሚከተለው ተብራርተዋል፡፡

### 4.1.1. በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ-ወጥ ግድያ)

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 "እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት" እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ኢትዮጵያ ፊርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳንም በአንቀጽ 6 (1) እና 9 (1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃልኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2 (1) እና 2 (2) ይደነግጋል፡፡

የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 "ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14  "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልፅ ደንግጓል፡፡ ኢትዮጵያም በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት እነዚህን ዓለም አቀፍ እና

አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች የተቀበለች እና የሐገሪቱ ሕግ አካል እንዲሆኑ ያደረገች ሀገር እንደመሆኗ፤ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል።

ይሁን እንጂ፣ መንግሥት እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌዎች ማስከበር ባለመቻሉ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ዜጎች ላይ በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት ተፈጽሟል። ከተራ ቁጥር 1 እስከ 35 ድረስ የቀረበው የሟቾች ዝርዝር ከሟቾች ቤተሰቦችና ምስክሮች የተገኘ ሲሆን፣ ከተራ ቁጥር 36 — 69 የቀረበው የሟቾች ዝርዝር ከቡራዩ ከተማ ፖሊስ መምሪያ በጽሑፍ በተገኘ ማስረጃ ላይ በመመሥረት የቀረበ ነው።

1. **ሟች እርዳቸው ሆርዶፋ፡-** *ዕድሜ* 30፣ *መስከረም* 04 *ቀን* 2011 *ዓ.ም* ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ በቡራዩ ገፈርሳ አካባቢ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እያለ ማንነታቸው ያልታወቀ፣ በቡድን የተደራጁ ሰዎች ቤቱን ሰብረው በመግባት በስለት ወግተው ባደረሱበት ጉዳት ሕይወቱ አልፏል። የሟች አስክሬን ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ተወስዶ ከተመረመረ በኃላ መስከረም 07 ቀን 2011 ዓ.ም ዊንጌት አካባቢ በሚገኘው ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተክተርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ መፈጸሙን የሟች ቤተሰቦችና የዓይን እማኞች ለኢሰመጉ አስረድተዋል። ሟች እርዳቸው ሆርዶፋ የሶስት ልጆች አባት ነበር።

2. **ሟች ባዩ ያደታ፡-** *ዕድሜ* 37፣ *መስከረም* 04 *ቀን* 2011 *ዓ.ም* ከጠዋቱ 2 ሰዓት አካባቢ በአዲስ አበባ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ አስኮ ብርጭቆ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በወቅቱ ማንነቱ ባልታወቀ ግለሰብ ግራ ፊቱ ላይ በገጀራ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል። አስክሬኑ ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ተወስዶ ከተመረመረ በኂላ ወደ ምዕራብ ሸዋ ዞን ግንደበረት ጊዮርጊስ ቤተክተርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ መፈጸሙን የሟች ቤተሰቦችና የዓይን እማኞች በአካባቢው ለተገኙ የኢሰመጉ የምርመራ ባለሙያዎች አስረድተዋል።

3. **ሟች አደቻ ቀበሎ፡-** *ዕድሜ* 38፣ *መስከረም* 04 *ቀን* 2011 *ዓ.ም* ከቀኑ 7 ሰዓት ተኩል አካባቢ በቡራዩ ጨረባ አካባቢ ባለው በመኖሪያ ቤቱ በራፍ ላይ እያለ ማንነታቸው ያልታወቁ በቡድን የተደራጁ ሰዎች በዱላ በመደብደብ ባደረሱበት ጉዳት ሕይወቱ አልፏል። አስክሬኑ ወደ ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል ተወስዶ ከተመረመረ በኃላ መስከረም 07 ቀን 2011 ዓ.ም አዲስ አበባ በሚገኘው ቅዱስ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ መፈጸሙን የሟች ቤተሰቦችና የዓይን እማኞች ገልጸዋል።

4. **ሟች ዳኒ ደንቃ፡-** *ዕድሜ* 18፣ *መስከረም* 05 *ቀን* 2011 *ዓ.ም* ከቀኑ 8 ሰዓት ላይ በቡራዩ ቤሮ ጠባሴ አካባቢ በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ እያለ ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች ተገድሏል። አስክሬኑ ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ተወስዶ ከተመረመረ በኃላ መስከረም 07 ቀን 2011 ዓ.ም ዊንጌት አካባቢ በሚገኘው የካቶሊክ መካነ-መቃብር ከቀኑ 9 ሰዓት የቀብር ስነ-ስርዓቱ መፈጸሙን ቤተሰቦችና የዓይን እማኞች ገልጸዋል።

5. **ሟች እርዳቸው ጋሞ፡-** *ዕድሜ* 46፣ *መስከረም* 04 *ቀን* 2011 *ዓ.ም* ከቀኑ 11 ሰዓት ላይ በቡራዩ ጮሪሳ በሚባል አካባቢ ማንነታቸው ባልታወቀ ሰዎች በዱላ ተደብድቦ ተጥሎ ሌሊቱን ሕይወቱ አልፏል። መስከረም 07 ቀን 2011 ዓ.ም ዊንጌት አካባቢ በሚገኘው ቅዱስ ጴጥሮስ ቤተ-ክተርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ መፈጸሙን የሟች ቤተሰቦችና የዓይን እማኞች ለኢሰመጉ አስረድተዋል። ሟች እርዳቸው ጋሞ ባለትዳርና የስድስት ልጆች አባት ነበር።

6. **ሟች ዊስፒታሌ ወንባ፡-** *ዕድሜ* 25፣ በቡራዩ ላንሱሲ በሚባል አካባቢ መስከረም 3 ቀን 2011 ዓ.ም. ማንነታቸው ባልታወቀ እና በቡድን በተደራጁ ሰዎች በስለት ባደረሱበት ጉዳት ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ተወስዶ ሊተርፍ ባለመቻሉ መስከረም 05 ቀን 2011 ዓ.ም ህይወቱ ሊያልፍ ችሏል።

7. **ሟች ቦንቃ ቦንቼ፡-** ዕድሜ 43፣ መስከረም 02 ቀን 2011 ዓ.ም ብርጭቆ ፋብሪካ አካባቢ ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች ሚስማር ባለው ዱላ ተደብድቦ በደረሰበት ጉዳት ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል። ሟች ባለትዳርና የአራት ልጆች አባት ነበረ።

8. **ሟች ገባ ገዝሞ ገና፡-** ዕድሜ 18፣ መስከረም 03 ቀን 2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 3 ሰዓት ላይ በቡራዩ ላንስሲ አካባቢ ማንነታቸው ባልታወቀ ግለሰቦች በዱላ ተደብድቦና በስለት ተወግቶ ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል።

9. **ሟች ቶማሴ ቶንጆ፡-** ዕድሜ 36፣ መስከረም 03 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 8 ሰዓት አስኮ ቀበሌ 15 እና 16 አካባቢ ማንነታቸው ያልታወቁ በቡድን የተደራጁ ሰዎች በዱላ በመደብደብ እና ጭንቅላቱን በመፈንከት ባደረሱበት ጉዳት ምክንያት ወደ ራስ ደስታ ሆስፒታል ተወስዶ ህክምና ቢደረግለትም ሕይወቱ ሊተርፍ አልቻለም። መስከረም 08 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 5 ሰዓት ላይ አዲስ አበባ በሚገኘው አቡነ ኃብተማርያም ቤተክተርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈፅሟል። ሟች ባለትዳርና የአንድ ልጅ አባት ነበረ።

10. **ሟች አማን አክመል፡-** ዕድሜ 26፣ መስከረም 03 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት ቡራዩ አካባቢ ማንነቱ ባልታወቀ ግለሰብ በጥይት አንገቱ ላይ ተመትቶ በደረሰበት ጉዳት ሕይወቱ አልፏል። አስክሬኑን ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ተወስዶ ከተመረመረ በኃላ ኮልፌ አካባቢ በሚገኘው የሙስሊም መቃብር መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም. የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈፅሟል።

11. **ሟች ቶማስ አይካ፡-** ዕድሜ 44፣ መስከረም 03 ቀን 2011 ዓ.ም ከምሽቱ 12 ሰዓት ቡራዩ ገፈርሳ አካባቢ የሽመና ሥራ ከሚሰራበት ቦታ ማንነታቸው ያልታወቁ ግለሰቦች ጎትተው በማውጣት፣ በስለት ወግተውት ሕይወቱ አልፏል። አስክሬኑን ወደ ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ተወስዶ ከተመረመረ በኃላ መስከረም 07 ቀን 2011 ዓ.ም አዲስ አበባ በሚገኘው ፊሊጶስ ቤተክርስትያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈፅሟል።

12. **ሟች አበባው ይመር፡-** በቀን ሥራ የሚተዳደር የ27 ዓመት ወጣት ነበር። መስከረም 04 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 7 ሰዓት ሲሆን ታሞ ከተኛበት መኖሪያ ቤቱ ማንነታቸው ያልታወቁ ሰዎች አውጥተው በመደብደብ እና በስለት በመውጋት ሕይወቱ እንዲያልፍ አድርገዋል። መስከረም 07 ቀን 2011 ዓ.ም ከጳውሎስ ሆስፒታል ቤተሠቦቹ አስክሬኑን በማውጣት ስርዓተ-ቀብሩም ኮልፌ በሚገኘው የሙስሊሞች መቃብር ተከናውኗል። ሟች ባለትዳር እና የአንድ አመት ከሰባት ወር ልጅ አባት ነበር።

13. **ሟች መንግሥቱ ደሴ፡-** በአገር አቋራጭ አውቶብስ ውስጥ በረዳትነት የሚሰራ የ30 አመት ወጣት ነበር። መስከረም 04 ቀን 2011 ዓ.ም በአካባቢው በነበረው ያለመረጋጋት ወቅት በጩቤ ተወግቶ ጉዳት ሲደርስበት መጀመሪያ በኮልፌ ጤና ጣቢያ ቀጥሎም ለከፍተኛ ህክምና ወደ አለርት ሆስፒታል ተወስዶ በህክምና ሲረዳ ቢቆይም ሕይወቱ አልፏል። አስክሬኑም ወደ ትውልድ ቦታው ጉራጌ ዞን ጉመር ወረዳ ተምበሮ መንደር ተልኮ የቀብር ስነ-ስርዓቱ መስከረም 6 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 7 ሰዓት በፕሮቴስታንት እምነት መቃብር ስፍራ ተፈጽሟል።

14. **ሟች ዓባይነህ አሰፋ፡-** በሽመና ሥራ የሚተዳደር የ18 ዓመት ወጣት ነበር። ሰኞ ጳጉሜ 5 ቀን 2010 ዓ.ም ምሽት ላይ ከቤት እንደወጣ ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች በዱላ ተደብድቦ ተገድሏል። ሟች ዓባይነህ ረቡዕ መስከረም 2 ቀን 2011 ዓ.ም ስርዓተ ቀብሩ በአስኮ ገብርኤል ቤተክርስትያን ተፈጽሟል።

15. **ሟች ኑሪ ከማል፡-** በቡራዩ ወረዳ አንፎ ጉዲና ቀበሌ ከ13 አመት በላይ የኖረ የ42 ዓመት በንግድ ሥራ የሚተዳደር ጎልማሳ ነበር። መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 3 ሰዓት መኖሪያ ቤቱን በርካታ ወጣቶች በመክበብ በዱላ እና ገጀራ ጭንቅላቱ ላይ እንዲሁም በድንጋይ ሰውነቱ

ላይ ተመትቶ በደረሰበት ጉዳት መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም ሕይወቱ አልፏል። መስከረም 8 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 8 ሰዓት በኮልፌ የሙስሊሞች መቃብር ስፍራ የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል።

16. **ሟች ባሪዲን ሀሰን፡-** መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ወደ አስኮ ሸጎሌ እየሄደ ሳለ በአካባቢው በነበረ ግጭት በድንጋይ፣ በዱላ እና በገጀራ ተመትቶ ህይወቱ አልፏል። መስከረም 06 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 10 ሰዓት ጃጅ የሙስሊሞች የመቃብር ስፍራ የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል።

17. **ሟች ወ/ሮ ፈትያ ሁሴን፡-** የ61 ዓመት የቤት እመቤት ሲሆኑ መስከረም 3 ቀን 2011 ዓ.ም ፒያሳ የአውቶብስ ተራ ታክሲ ለመያዝ ተሰልፈው ነበር። በዚህ ወቅት ሳጅን ከድር በተባለ የፖሊስ አባል ጭንቅላታቸው ላይ በጥይት ተመተው አቤት ሆስፒታል ሕክምና ቢደረግላቸውም በእለቱ ሕይወታቸው አልፏል። በማግስቱ መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 10 ሰዓት ኮልፌ የሙስሊሞች መቃብር ስፍራ የቀብር ስርዓታቸው ተፈጽሟል።

18. **ሟች ቦንቃ ቦንቹ፡-** በቀን ሥራ የሚተዳደር የ45 ዓመት ጎልማሳ ነበር። መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት ማንነታቸው ባልታወቁ ወጣቶች ካኦጂጂ ዱቄት ፋብሪካ አካባቢ ጭንቅላቱን በድንጋይ ተመትቶ ጳውሎስ ሆስፒታል ሲደርስ ሕይወቱ አልፏል። የቀብር ስነ-ስርዓቱም መስከረም 6 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት በአስኮ ገብርኤል ቤተ-ክርስቲያን ተፈጽሟል።

19. **ሟች ወልዴ ኡሬ፡-** በሽመና ሥራ የሚተዳደር የ24 ዓመት ወጣት ነበር። ዓርብ መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ከጠዋቱ አራት ሰዓት ገጀራ፣ ዱላ እና ፌሮ በያዙ ወጣቶች ተደብድቦ ተገድሏል። መስከረም 8 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት ጴጥሮስ ቤተ-ክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል።

20. **ሟች ሰለሞን ካሳሁን፡-** የ17 ዓመት ተማሪ ነበር። ረቡዕ መስከረም 2 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት ላይ ኮልፌ ወረዳ 15 አወልያ ኬላ መውጫ ላይ ባልታወቁ ወጣቶች በድንጋይ ጭንቅላቱን ተመትቶ ተገድሏል።ፖሊስ አስክሬኑን ወደ አቤት ሆስፒታል ወስዶት ምርመራ ከተደረገለት በኋላ መስከረም 5 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 8 ሰዓት ሸጎሌ ኪዳነ-ምህረት የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል።

21. **ሟች ታይሰን ገዬ፡-** መስከረም 2 ቀን 2011 ዓ.ም ከጠዋቱ 4 ሰዓት ብዛት ያላቸው ወጣቶች "ዶርዜ ይውጣ" በማለት ባስነሱት ረብሻ በሽመና ሥራ ይተዳደር የነበረውን የ36 ዓመት ወጣት በዱላ እና በገጀራ ተመትቶ ተገድሏል። የቀብር ስነ-ስርዓቱም መስከረም 4 2011 ዓ.ም. ከቀኑ 8 ሰዓት ፊሊፖስ ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል።

22. **ሟች አብዮት ቢሆነኝ፡-** በሽመና ሥራ የሚተዳደር የ32 ዓመት ወጣት ነበር። መስከረም 1 ቀን 2011 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 1 ሰዓት አካባቢ መጣሁ ብሎ ቡራዩ ጮሪሳ አካባቢ ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ እንደወጣ የተደራጁ የአካባቢው ወጣቶች በዱላ ደብድበውት ሕይወቱ አልፏል። መስከረም 2 ቀን 2011 ዓ.ም ጮሪሳ ሚካኤል የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል። ሟች ባለትዳር እና የ3 ልጆች አባት ነበር።

23. **ሟች ሳላዲን ከድር፡-** በንግድ ስራ ይተዳደር የነበረ የ35 ዓመት ወጣት ነበር። መስከረም 3 ቀን 2011 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 2 ሰዓት አካባቢ ወደ አስር የሚጠጉ ወጣቶች መኖሪያ ቤቱን ሰብረው በመግባት የቤት ንብረት ከመዝረፍና በማውደማቸው በተጨማሪ ቤት ውስጥ በነበረችው ባለቤቱ ላይ ድብደባ ፈጽመዋል። እርሱም ተደብድቦ ሕይወቱ አልፏል። የሟች አስከሬን መስከረም 5 ቀን 2011 ዓ.ም አሸዋ ሜዳ ኮልፌ የሙስሊሞች መቃብር የቀብር ስነ-ስርዓቱ የተፈፀመ ሲሆን ባለትዳርና የ1 ልጅ አባት ነበር።

24. **ሟች ቶዳኬ ቁስ፡-** በሽመና ሥራ ይተዳደር የነበረ የ26 ዓመት ወጣት ነበር። መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ማንነታቸው ያልታወቁ ወጣቶች ቡራዩ ገፈርሳ አካባቢ ባደረሱበት የዱላ ድብደባ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት ለህክምና ወደ ሆስፒታል ቢወሰድም ማትረፍ ስላልተቻለ ህይወቱ መስከረም 6

ቀን 2011 ዓ.ም ህይወቱ አልፏል፡፡ መስከረም 8 ቀን 2011 ዓ.ም አዲስ አበባ ሽሮ ሜዳ በሚገኘው ቁስቋም ማሪያም ቤተ-ክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል። ሟች ባለትዳር እና የ1 ልጅ አባት ነበር፡፡

25. **ሟች ዳንኤል ዲንቃ፦** በቀን ሥራ ይተዳደር የነበረ የ23 ዓመት ወጣት ነበር። መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ከቀኑ በ9 ሰዓት በቆንጨራ ግንባሩን ተመትቶ ህይወቱ አልፏል። የቀብር ስነ-ስርዓቱም መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 6 ሰዓት አዲስ አበባ በሚገኘው ዊንጌት ጴጥሮስ ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል።

26. **ሟች አብዲ ሽኩር ተስፋዬ፦** ጸጉር በማስተካከል ሥራ ይተዳደር የነበረ የ27 ዓመት ወጣት ነበር። መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ሶራምባ (ብርሃኑ ሜዳ) አካባቢ ከቡራዩ በመጡ ወጣቶች ጭንቅላቱን ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል። መስከረም 6 ቀን 2011 ዓ.ም ጉራጌ ዞን እነሞር የሙስሊሞች መቃብር የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈጽሟል። ሟች ባለትዳር እና የ 2 ልጆች አባት ነበር።

27. **ሟች ወ/ሮ አለውያስማን፦** ዕድሜ 25፣ መስከረም 05 ቀን 2011 ዓ.ም ቅዳሜ ከረፋዱ 5 ሰዓት ላይ በመኖሪያ ቤቷ ቡራዩ (ጉጂ) ጊቢ ውስጥ እንዳለች ማንነቱ በማይታወቅ ሰው በተተኮሰ ጥይት ተመትታ ሕይወቷ አልፏል። የቀብር ስነ-ስርዓቷም መስከረም 06/2011 ዓ.ም በኮልፌ የሙስሊሞች መቃብር ተፈጽሟል።

28. **ሟች ባይከዳኝ በርገና ወንበራ፦** ዕድሜው 42 ዓመት እና በሽመና የሚተዳደር ጉልማሳ ሲሆን በ4/1/2011 ዓ.ም ከቀኑ በ9 ሰዓት በተደራጁ ወጣቶች አንገቱን በገጀራ ተመትቶ ህይወቱ አልፏል። የቀብር ስነ-ስርዓቱም ዊንጌት አካባቢ በሚገኘው መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በ07/01/2011 ዓ.ም ተፈፅሟል።

29. **ሟች መሰለ ሮቢ፦** እድሜው 47 በሽመና የሚተዳደር ባለትዳር እና የ5 ልጆች አባት ነበር። መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ቡራዩ ዱሩ ልዩ ቦታው እርጎ ሰፈር የሚባል አካባቢ ከቀኑ በ9 ሰዓት ላይ በተደራጁ ወጣቶች በገጀራ ተመትቶ ህይወቱ አልፏል። በ07/01/2011 ዓ.ም ዊንጌት አካባቢ መድኃኔዓለም ቤተ-ክርስቲያን የቀብር ስነስርዓቱ ተፈፅሟል።

30. **ሟች እርዳቸው ፋኖ፦** እድሜው 46 ዓመት በጉልበት ሥራ የሚተዳደር ባለትዳር እና የ6 ልጆች አባት ነበር። ቡራዩ ጮሪሳ የሚባል ቦታ በ4/1/2011 በገጀራ ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል። በ07/01/2011 ዓ.ም ዊንጌት አካባቢ መድኃኔዓለም ቤተ-ክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈፅሟል።

31. **ሟች ስንታየሁ ፋኖ፦** በሽመና የሚተዳደር ባለትዳር እና የ3 ልጆች አባት ነበር። ቡራዩ ዱሩ በተባለ ቦታ በ04/01/2011 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት በተደራጁ ወጣቶች በገጀራ አንገቱ ተመትቶ ህይወቱ አልፏል። በ07/01/2011 ዓ.ም ዊንጌት አካባቢ መድኃኔዓለም ቤተ-ክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈፅሟል።

32. **ሟች ጋሻው ተሰማ፦** ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ የሺ ደበሌ አካባቢ በታክሲ ተራ ማስከበር ሥራ ይሰራ የነበረ ወይብላ ማርያም ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ተመቶ ሕይወቱ አልፏል። ከቡራዩ ከተማ ፖሊስ መምሪያ የተገኘ ማስረጃ እንደሚያሳየው በወይብላ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን የቀብር ስነ-ስርዓቱ ተፈፅሟል።

33. **ሟች ሀብታሙ ሽፈራው፦** በኮልፌ 18 ማዞሪያ አካባቢ ይኖር የነበረና በቀን ሥራ ይተዳደር የነበረ የ33 ዓመት ወጣት ነበር። መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም 18 ማዞሪያ አካባቢ ከቀኑ 10 ሰዓት ማንነታቸው ባልታወቁ ወጣቶች በዱላና በድንጋይ ተመትቶ ጳውሎስ ሆስፒታል ቢገባም ሕይወቱ መስከረም 10 ቀን 2011 ዓ.ም አልፏል፡፡ የቀብር ስነ-ስርዓቱም መስከረም 11/2011 ዓ.ም ኮልፌ አካባቢ በሚገኘው ፊሊፖስ ቤተ-ክርስትያን የመቃብር ስፍራ ተፈፅሟል፡፡

34. **ሟች በረከት ቡዝኣላንዳ፡-** የ25 ዓመት ተማሪ ነበር። መስከረም 05 ቀን 2011 ዓ.ም ማንነታቸው ባልታወቁ ወጣቶች በአካፋ ጭንቅላቱን ተመትቶ ሕይወቱ አልፏል። መስከረም 9 ቀን 2011 ዓ.ም ቁስቋም ቤተ-ክርስትያን በሚገኘው የመቃብር ስፍራ ተፈፅሟል።

35. **ሟች ሳዳ ሠረቶ ሣንቃ፡-** በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 6 ውስጥ በሽመና ሥራ ይተዳደር የነበረ የ27 ዓመት ወጣት ነበር። መስከረም 07 ቀን 2011 ዓ.ም የአካባበቢው ወጣቶች ‹‹ዛሬ ሥራ መስራት አይቻልም›› በማለት የሽማ መሥሪያ ቤታቸው እንዲዘጋ አደረጉ። በዚያ ምክንያት ሟች ከሰላማዊ ሰልፈኞች ጋር ተቀላቅሎ ከሽሮ ሜዳ ተነስተው አራት ኪሎ ሲደርሱ የመከላከያ ሰራዊት አባላት አስቆሟቸው። ከዛም በሌላ መንገድ ከሌሎች ሰልፈኞች ጋር በመሆን ወደ ኢትየጵያ ቴሌቭዥን አመሩ። ነገር ግን ከረፋዱ 5፡30 ላይ ልደታ ክፍለ ከተማ ሐራምቤ ሆቴል አጠገብ የመከላከያ ሰራዊት አባላት ሰልፈኞቹን መሬት ላይ ተቀመጡ ብለዋቸው ሰልፈኞቹ ቢቀመጡም ከአንድ የመከላከያ ሰራዊት አባል በተተኮሰ ጥይት ግራ ታፋውን እና ደረቱ ላይ በጥይት ተመትቶ ዘውዲቱ ሆስፒታል በግምት 6 ሰዓት ላይ ለህክምና ቢገባም ሕይወቱ ሆስፒታል ውስጥ አልፏል። የቀብር ስነ-ስርዓቱም በደብረ ቁስቋም ቤተ-ክርስቲያን መስከረም 09 ቀን 2011 ዓ.ም ተፈፅሟል። ሟች ባለትዳርና የአንድ ልጅ አባት ነበር።

36. **ሟች ተሾመ ድሪባ፡-** ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 13 ሎዛ ማርያም ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን የኮልፌ አካባቢ ፖሊስ በጽሁፍ ገልጿል።

37. **ሟች አዱባ ታዲቻ፡-** በ07/01/11 ዓ.ም ሱቂ ማርያም ቤተ-ክርስቲያን አካባቢ በኮልት ሽጉጥ ተመቶ መገደሉን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ፖሊስ በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

38. **ሟች መኳንንት ሞኝሆ፡-** በ08/01/2011 ዓ.ም ምሽት 12፡30 ወረዳ 11 ላፍቶ አባሻውል ድልድይ አካባቢ ተደብድቦ ሕይወቱ ማለፉን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ፖሊስ በጽሁፍ ገልጾልናል።

39. **ሟች ከድር ናስር፡-** ዕድሜ 30፣ አዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 07 ገነት ት/ቤት አካባቢ በ03/01/11 ዓ.ም ከቀኑ 4 ሰዓት በድንጋይ ጭንቅላቱ ላይ ተመትቶ ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ለኢሰመጉ ገልጿል።

40. **ሟች ደገፉ አለሙ፡-** ዕድሜ 17፣ አዲስ አበባ ከተማ ጎጃም በረንዳ አካባቢ በ 03/01/11 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት በድንጋይ ግንባሩ ላይ ተጎድቶ ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

41. **ሟች ሲሳይ ሴንሳ፡-** ዕድሜ 65፣ መኖሪያአድራሻው አዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 8 የቤት ቁጥር 957 የሆነ በ04/01/2011 ዓ.ም ከቀኑ 5 ሰዓት ኮልፌወረዳ 8 የሺ ደበሌ አካባቢ በዱላ ተመተው ሕይወታቸው ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

42. **ሟች አዲሱ ደጀኔ፡-** ዕድሜ 25፣ ኮልፌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 11 ኢንዱስትሪ መንደር በ 04/01/11 ዓ.ም ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት በድንጋይ ጭንቅላቱ ላይ በደረሰ ጉዳት ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

43. **ሟች ጌታቸው ከበደ፡-** በኮልፌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 18 ማዞሪያ በ 04/01/11 ዓ.ም ከቀኑ 9 ሰዓት በድንጋይ ግንባሩን ተመትቶ ሕይዎቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

44. **ሟች ሚፍታ ሁሴን፡-** ዕድሜ 35፣ ኮልፌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 8 ወይብላ ማርያም በ04/01/2011 ዓ.ም ከቀኑ 12 ሰዓት በድንጋይ ግንባሩን ተመትቶ ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ለኢሰመጉ ገልጿል።

45. **ሟች በላይ በቾ፡-** አድራሻ ቡራዩ ሬሊ ዶሮ እድሜ 24 ኮልፌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 ልኳንዳ በ04/01/2011 ዓ.ም ከሌሊቱ 6:30 በድንጋይ ጭንቅላቱ ተመትቶ ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

46. **ሟች ዳኜ ፊየራ፡-** እደሜ 25፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ጀሞ አካበቢ በ04/01/2011 ዓ.ም ከምሽቱ 1:15 በድንጋይ ጭንቅላቱ ላይ በደረሰ ጉዳት ሕይዎቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ለኢሰመጉ ገልጿል።

47. **ሟች ሲሳይ ወልዱ፡-** እድሜ 29፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ሐራንቤ ሆቴል በ07 01/2011 ዓ.ም ከቀኑ 4 ሰዓት በክላሽ ጥይት ግራ ታፋው ላይ ተመትቶ ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

48. **ሟች አዱኛ ዳጫ፡-** እድሜ 20፣ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 ሱቂ ማርያም አካባቢ በ07/01/2011 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት በሽጉጥ ጥይት ጭንቅላቱ ተጎድቶ ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

49. **ሟች መሰለ ሎሬንሶ፡-** እድሜ 20፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 ሐራንቤ ሆቴል በ 07/01/11 ዓ.ም ከቀኑ 4 ሰዓት በጥይት በቀኝ በኩል ከባቱ ስር ተመትቶ ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

50. **ሟች አበበ አሣ፡-** እድሜ 25፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 ሐራምቤ ሆቴል በ 07/01/2011 ዓ.ም ከቀኑ 4 ሰዓት በክላሽ ጥይት አንገቱ ስር ተመትቶ ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በጽሁፍ ለኢሰመጉ ገልጿል።

51. **ሟች ባንተላይ ተስፋው፡-** እድሜ 40፣ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ራስ ደስታ አካባቢ በ03/01/2011 ዓ.ም ከምሽቱ 3:30 በድንጋይ ጭንቅላቱ ላይ በደረሰ ጉዳት ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ገልጾልናል።

52. **ሟች መሀመድ አክመል፡-** እድሜ 35፣ ኮልፌ ክፍለ ከተማ ካኦ ጂ ጂ አካባቢ በ04/01/11 ዓ.ም ከቀኑ 5 ሰዓት በዱላ ጭንቅላቱ ተጎድቶ ሕይዎቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን በደብዳቤ ለኢሰመጉ ገልጿል።

53. **ሟች መኩሪያ አጀማ፡-** አድራሻ ቡራዩ ከተማ ገፈርሳ ጉጅ ቀበሌ፣ እድሜ 25፣ ኮልፌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 12 ልኳንዳ በ04/01/2011 ዓ.ም ከቀኑ 12 ሰዓት በስለት ጭንቅላቱ ተሰንጥቆ ሕይወቱ ያለፈ መሆኑን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ለኢሰመጉ ገልጿል።

54. **ሟች ጉደታ ቦንሳ፡-** በ04/01/2011 ዓ.ም ከቀኑ 7:15 በድንጋይ ጭንቅላቱ ተጎድቶ ሕይወቱ ማለፉን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ለኢሰመጉ ገልጿል።

55. **ሟች አርጃ አንጎታ**
56. **ሟች አለማየሁ ቦቃ**
57. **ሟች አስሬ ጎታሶሬ**
58. **ሟች ጮራ ጫላ**
59. **ሟች አንትሄ ማጫ**
60. **ሟች ሙዲን መሀመድ ሺፋ**
61. **ሟች ወሌ ወጋየሁ**
62. **ሟች ብርሀኑ ሚናቴ**
63. **ሟች ማትያስ ዋጃሮ**
64. **ሟች የሽሮ ወናቃ**

65. ሟች አለዊያ ሰማን
66. ሟች ጋሻው ተሰማ
67. ሟች ተፈሪ ለማ
68. ሟች አድማሶ ተገኝ
69. ሟች ጊቦ በደዳ

**በአዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ አካባቢዎችና በቡራዩ ከተማና አካባቢው የተገደሉ ሰዎች ፎቶግራፎች ፡-**



እርዳቸው ጋሞ



ቶዳኬ ቂስ



ባይከዳኝ በርገና



ሀብታሙ ሽፈራው



መንግስቱ ደሴ



በረከት ቡዝአ



ፈትያ ኑሪ



ሁሴን ቦንቃ ቦንቼ



ኑሪ ከማል



አማን አክመል



ቶማስ አይካ



ባዩ ያደታ



ሰዓዳ ሰሪቶ



በረዲን ሀሰን



ዳንኤል ዳንቃ



እርዳቸው ወርዶፋ



አብዲ ሽኩር ተስፋዮ

### 4.1.2. የአካል ጉዳት (ማቁሰል)

ዓለም አቀፉ የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች የቃል-ኪዳን ስምምነት በአንቀጽ 9 ሥር እንደሚደነግገው ማንኛውም ሰው አከላዊ ደህነነቱ የተጠበቀ መሆን ይገባዋል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥትም በአንቀጽ 16 ሥር ‹‹ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው›› ሲል ይደነግጋል፡፡ የሰዎች የአካል ደኅንነት የመጠበቅ መብት የማይደፈርና የማይገሠሥ መሆኑንም የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 14 ያረጋግጣል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌን መንግሥት ባለማስከበሩ ምክንያት በሚከተሉት ግለሰቦች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

ከጳጉሜ 3 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ በቡራዩ ከተማና በተለያዩ ቀበሌዎች ብሔር ተኮር ጥቃት በመፈጠሩ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ሥም ዝርዝር ከዚህ በታች ቀርቧል።

1. **አቶ ሰሎሞን መሬቻ፡-** እድሜ 36፣ በሽመና የሚተዳደር ባለትዳር ሲሆን ለኢሰመጉ እንዳመለከተው ቡራዩ አካባቢ መኖር ከጀመረ ከ20 ዓመት በላይ ነው። አሁን ተከራይቶት ያለበትን ቤት ላለፉት 6 አመታት ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር ኖሮበታል። መስከረም 4 2011 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰዓት ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች በቢላዋ ጭንቅላቱንና ጀርባው ላይ ተወግቶ ጉዳት ደርሶበታል።

2. **አቶ ቦጋለ ጎይዞ፡-** እድሜ 57፣ በሽመና ሥራ የሚተዳደሩ እና በቡራዩ አካባቢ የሚኖሩ ሲሆን ቡራዩ ቀበሌ መልካ ገፈርሳ ጎጥ መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ማንነታቸው ባልታወቁ ወጣቶች ከጠዋቱ 4 ሰዓት በዱላ እና በፌሮ ድብደባ ተፈጽሞባቸዋል።

3. **አቶ ጎልጌ ጎቡና**፡- እድሜ 50፣ በሽመና የሚተዳደሩ በሰበታ ጀሞ ቀበሌ የሚኖሩት አዛውንት እንዳመለከቱት መስከረም 4 ቀን 2011 ዓ.ም ከቀኑ 8 ሰዓት ሰበታ ጀሞ በመኖሪያ ቤታቸው እንዳሉ ማንነታቸው ባልታወቁ ወጣቶች ድብደባ ተፈፅሞባቸዋል።

4. **አቶ ጋሞ ጋፌ፡-** በቡራዩ ወረዳ በሽመና ሥራ እየተዳደረ የሚኖር እድሜው 38 ባለትዳር እና የ3 ልጆች አባት ነው። ሀሙስ በ03/01/2011 ዓ.ም ከቀኑ11 ሰዓት ማንነታቸው የማይታወቁ ወጣቶች ጭንቅላቱ ላይ በዱላና በድንጋይ ተመትቶ ጉዳት ደርሶበታል።

5. **አቶ ጦሳ አዲያስዋራን፡-** እድሜ 28 ሲሆን ሰበታ ወረዳ ቀበሌ 08 ነዋሪ ሲሆን በ6/01/2011 ዓ.ም ከምሽቱ 1 ሰዓት ተኩል ሲሆን ማንነታቸው ባልታወቁ ወጣቶች በቆንጨራና በዱላ ተመትቶ ጉዳት ደርሶበታል።

6. **አቶ ጣሰው ጨሬቦ ፀጋዬ፡-** በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 1 **የሚኖር** በሽመና ሥራ የሚተዳደር የ45 ዓመት ጎልማሳ ነው። በ04/01/2011 ዓ.ም ላይ ቡራዩ ከተማ ከምሽቱ 4 ሰዓት ላይ ባልታወቁ ሰዎች በዱላና በገጀራ ድብደባ ተፈፅሞበታል።

7. **ወ/ሮ ዲኮሬ አመላ ኩላ፡-** በቡራዩ ድሬ ቀበሌ የሚኖሩ የ40 ዓመት የቤት እመቤት ሲሆኑ መስከረም 3 2011 ዓ.ም ከቀኑ 5 ሰዓት በቡራዩ ከተማ ድሬ ሰፈር ባልታወቁ ወጣቶች ጀርባቸውንና እግራቸው ላይ ተደብድበው ጉዳት ደርሶባቸዋል።

8. **አቶ ሀብታሙ ጣሌ ጠንጋ፡-** ጉለሌ ክ/ከተማ በወረዳ 6 ቀበሌ 18 በሽመና ሥራ እየተዳደረ የሚኖር የ24 ዓመት ወጣት ነው። ሰኞ መስከረም 7 ቀን 2011 ዓ.ም ኢትዮጵያ ብሮድካስተንግ ኮርፖሬት (ኢቢሲ) አካባቢ ማንነቱ ባልታወቀ የመከላከያ ሰራዊት አባል በተተኮሰ ጥይት ግራ ታፋው ላይ ጉዳት ደርሶበታል።

9. **አቶ ወሡኑ ወጋ ወልዴ፡-** በቡራዩ ቀበሌ 02 የሚኖሩና በሽመና ስራ የሚተዳደሩ የ43 ዓመት ጎልማሳ ናቸው። መስከረም 3 ቀን 2011 ዓ.ም ከረፋዱ 3 ሰዓት ቡራዩ ከተማ ውስጥ ማንነታቸው ባልታወቁ ወጣቶች በተፈፀመባቸው ከፍተኛ ድብደባ የቀኝ እግራቸው ከጉልበታቸው በታች ስብራት ደርሶበታል።

### 4.1.3. ከቤት ንብረት መፈናቀል

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 40 ሥር ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ እንደሚከበርለት ይደነግጋል። ሆኖም ከእዚህ ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ በተቃራኒው በወቅቱ በነበረው ክስተት በርካታ ዜጎች የግል ንብረታቸው ከሆነው መኖሪያ ቤታቸው ያለ አግባብ ተፈናቅለዋል።

- **በወቅቱ ተፈናቃዮቹ ተጠልለው ይገኙባቸው የነበሩ መጠለያዎች**

ከ06/01/2011 ዓ.ም ጀምሮ ከቡራዩ ከተማ የተለያዩ አካባቢዎች በግጭቱ ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎች ተጠልለውባቸው የነበሩ ተቋማት፡-

1. ፊሊጶስ ት/ቤት
2. ወረዳ 11 ወጣት ማዕከል
3. ቃሌ ት/ቤት
4. አስኮ ት/ቤት
5. ብስራት ት/ቤት
6. ሚኪሊ ላንድ ት/ቤት
7. ጉለሌ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት
8. ወረዳ 8 ወጣት ማዕከል፡- ከሶር አምባ፣ ቤሩ፣ አሸዋ ሜዳ፣ ፍሪዶር፣ ከታ፣ ገብርኤል፣ ቡራዩ
9. ሽሮ ሜዳ አካባቢ ወረዳ 1 እና ወረዳ 6 ወጣት ማዕከል

ከ06/01/2011 ዓ.ም ጀምሮ 15000 (አስራ አምስት ሺ.ህ) ተፈናቃዮች ተጠልለው ቆይተውና በአዲስ አበባ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሠራተኞችና በአዲስ አበባ ህዝብ የተለያዩ የምግብ፣ የውሃና የአልባሳት እርዳታ ከተደረገላቸው በኋላ ት/ቤቶች ሲከፈቱ ከመስከረም 18/2011 ዓ.ም ጀምሮ ወደ ተፈናቀሉበት ቦታ ተመልሰዋል፡፡

በቡራዩ እና አከባቢው በተፈጠረው ብሔርን መሰረት ያደረገ ጥቃት ምክንያት የተፈናቀሉ አባወራዎች ብዛት ወንድ 2563፣ ሴት 348 ድምር 2911 ሲሆን፤ ጠቅላላ የቤተሰብ ብዛት ወንድ 5462፣ ሴት 5212 ድምር 10674 ናቸው፡፡

**በተፈጠረው ችግር ምክንያት የንብረት ውድመት የደረሰባቸው ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም የሚያስፈልግ የገንዘብ መጠን፤**

1. ለመኖሪያ ቤት ማሠራትና ጥገና 250 ጉዳት 5,409,353 ብር
2. የሽመና ሥራ መስሪያ የወደመባቸው 1082 የሽመና ዕቃ መግዣ 5,409,353 ብር
3. የ60 ሰዎች ሱቅና ሽቀጣ ሽቀጥ የተዘረፈባቸውን ለመተካት 2,509,986 ብር
4. የ500 ሰዎች የወደመ የተለያዩ የቤት ቁሳቁሶች መተኪያ 4,753,945 ብር
5. የ600 ሰዎች አልባሳት በመዘረፉ ለመተካት 3,006,945
6. የ2000 ሰዎች የመስሪያ ገንዘባቸው ስለተዘረፈ ለመተካት 4,892,702 ብር
7. ሙሉ ለሙሉ ንብረታቸው የወደመባቸው 20 ሰዎች ለማቋቋም 1,000,000 ብር
8. 149 ከባድ ጉዳትና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው 3,725,000 ብር
9. 6 መኪና የመሰባበር ጉዳት ለደረሰበት ማስተካከያ 3,87000 ብር
10. ለወላዶች፣ ለህጻናትና ለአረጋዊያን ምግብ አቅርቦት 350,000 ብር
11. መሰረተ ልማት፣ ውኃ፣ መብራትና ት/ቤቶችን ለማስተካከል 6,500,000 ብር

በድምሩ **41,427,284** (አርባ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሃያ ሰባት ሺ ሁለት መቶ ሰማንያ አራት ብር) ለመልሶ ማቋቋሚያ እንደሚያስፈልግ ተፈናቃዮችን ለመደገፍ የተቋቋመው ኮሚቴ ይህን ሪፖርት ለማዘጋጀት ምርመራ በተደረገበት ወቅት ገልጾ ነበር፡፡

## 4.2. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ሰሜን ሸዋ ዞንና የኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች ውስጥ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

*መግቢያ*

በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች አልፎ አልፎ የሚነሱ ግጭቶች ቢኖሩም ባለፉት ጊዜያት በኃይማኖት መሪዎችና በሀገር ሽማግሌዎች ችግሮቹ ሲፈቱ ኖረዋል፡፡ ዳሩ ግን ባለፉት 27 ዓመታት በተለያየ ጊዜ ብሔርን መሠረት ያደረጉ ግጭቶችና ጥቃቶች በተለያዩ አካባቢዎች በመከሰታቸው ዘርፈ ብዙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል፡፡

ለብሔር ተኮር ጥቃቶችና ግጭቶች በቂ ትኩረት ባለመሰጠቱ፣ ይህንኑ ለመከላከልም አስፈላጊው የሕግና ተቋማዊ ስራ በመንግስት በኩል ባለመሠራቱ በመላ ሀገሪቱ ቀውሱ ተባብሶ አሁን አስፈሪ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ እነዚህ ግጭቶች ያስከተሉትን ሰብዓዊና ቁሳዊ ጥፋቶችን ለመረዳት ኢሰመጉ ካወጣቸው መግለጫዎች መካከል ለአብነት 141ኛ ልዩ መግለጫን በመመልከት ለመረዳት ይቻላል፡፡[1]

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰሜን ሸዋ ዞንና በኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን ውስጥ የሚኖሩ አርሶ አደሮችና የከተማ ነዋሪዎች ለዘመናት በባህል፣ ጋብቻ የተሳሰሩ ወንድማማች ህዝቦች ናቸው፡፡ ከዚህ ባሻገር በሳምንት ውስጥ ለአምስት ጊዜያት ያህል በተለያዩ ቦታዎች በሚቆሙ ትልልቅ ገበያዎች የአካባቢው ኦሮምኛና አማርኛ ተናጋሪ ነዋሪዎች እየተገናኙ በፍቅርና በሰላም ሲገበያዩ የኖሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶቹ የተፈጸመበት የኤፍራታ ግድም ወረዳ ዋና ከተማ አጣዬ ከአዲስ አበባ ከተማ ያለው ርቀት 280 ኪ.ሜ ሲሆን በውስጡም ማጀቴ እና ካራቆሬ የሚባሉ ቀበሌዎች ይገኛሉ፡፡

### 4.2.1. የጥቃቱ መነሻ ታሪክ

የኢሰመጉ ምንጮች እንደገለጹት ከሁለት ዓመታት በፊት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን ሦስት ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ቦራ፣ ፉርሲና ጀውሃ በሚባሉ ቀበሌዎች ‹‹የኦነግ ናቸው›› ለተባሉ ታጣቂዎች ሥልጠና ይሰጥ እንደነበርና ይህን መረጃ ማግኘቱን የሚገልጸው የሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደር ጉዳዩ ለአካባቢው የጸጥታ ስጋት ሊፈጥር ይችላል በሚል ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ቢያመለክትም አጥጋቢ ምላሽ እንዳልተሰጠው በወቅቱ በአማራ ክልል ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ቀርቦ አስታውቋል፡፡ ኢሰመጉም በጉዳዩ ላይ ማስረጃ እንዲሰጠው ለሰሜን ሸዋ ዞን አስተዳደርና ለሰሜን ሸዋ ዞን ፖሊስ መምሪያ በደብዳቤና በስልክ በተደጋጋሚ ቢጠይቅም ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ መልስ አላገኘም፡፡

የአማራ ክልላዊ መንግሥት ባለሥልጣናት በወቅቱ ለብዙኃን መገናኛ በተናገሩት መሠረትና የምስክርነት ቃላቸውን ለኢሰመጉ የሰጡ የአካባቢው ነዋሪዎች እንደገለጹት መጋቢት 29 ቀን 2011 ዓ.ም የጸጥታ አካላትን የደንብ ልብስ የለበሱ ‹‹የኦነግ ናቸው›› የተባሉ ታጣቂዎች ማጀቴ አካባቢ በሚገኝ የእርሻ ማሳ ላይ ተሠማርተው በነበሩ ገበሬዎች ላይ ተኩስ በመክፈት 19 ሰዎች ገድለዋል፣ 23 ሰዎችን

[1]የኢሰመጉ ድረ ገፅ www.ehrco.org ይጎብኙ፡፡

አቁስለዋል። በማሳው ላይ የነበረ ለገበያ የተዘጋጀ 625 ኩንታል ሽንኩርት ዘርፈዋል፣ 47 የውኃ ሞተሮች ወስደዋል። እነዚሁ ታጣቂዎች መጋቢት 28 ቀን 2011 ዓ/ም ጨፋ ወረዳ ቀጨማ የሚገኘውን የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ለመዝረፍና ለማቃጠል ሙከራ ማድረጋቸውንና ቤተ-ክርስቲያኑን ከጥፋት ለመከላከል ከሞከሩ ነዋሪዎች መካከል አራት ሰዎች መገደላቸውን ለኢሰመጉ የምስክርነት ቃላቸውን የሰጡ የአካባቢው ነዋሪዎች ገልጸዋል።

ሰኔ 29 ቀን 2010 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተደረገውን የፖለቲካ ለውጥ በመደገፍ በርካታ ሰዎች የተሳተፉበት ሰልፍ በተካሄደበት ወቅት ታጣቂዎች የአጣዬ ሚሊሻ ፅ/ቤት መጋዘን በማጥቃት የጦር መሳሪያ መዝረፋቸውን የኤፍራታና ግድም ወረዳ አስተዳደር ለኢሰመጉ ገልጿል። ታጣቂዎቹ የአንድ ፖሊስ ሕይወት አጥፍተው ሁለት ፖሊሶች አቁስለው እንደነበርና መንግስት ባደረገው ክትትል ወንጀሉን የፈጸሙት ግለሰቦች ተይዘው እንደታሰሩ ኢሰመጉ አረጋግጧል። በወቅቱ በነበረው ክስተት የተፈጸሙት የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችም እንደሚከተለው ተብራተዋል።

### 4.2.2. በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ-ወጥ ግድያ)

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 "እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነቱ የመጠበቅ መብት" እንዳለው ያረጋግጣል። ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳንም በአንቀጽ 6 (1) እና 9 (1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2 (1) እና 2 (2) ይደነግጋል። የአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 "ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደህንነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት ይገባል። ማንም እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፍገው አይገባም" ይላል።

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14 "ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና የነጻነት መብት አለው" ሲል ይደነግጋል። በተመሳሳይ የሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 15 ማንም ሰው በህይወት የመኖር መብት እንዳለውና ሕግ ከሚደነግገው ውጪ የመኖር መብቱን ሊያጣ እንደማይችል ተመላክቷል። ኢትዮጵያም እነዚህን ዓለም አቀፍ እና አህጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች የተቀበለች ሀገር እንደመሆኗ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል።

እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌዎች በየደረጃው ያሉ የመንግስት አካላት ማስከበርና መጠበቅ ባለመቻላቸው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ሸዋ ዞን ኤፍራታ ግድም ወረዳ በአጣዬ፣ በማጀቴና ካራቆሬ አካባቢዎች እንዲሁም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ ቀበሌዎች ነዋሪ በነበሩ ዜጎች ላይ ግድያና የአካል ጉዳት ተፈጽሟል።

በአ/ብ/ክ/መ/ ሰሜን ሸዋ ዞን የአጣዬ ከተማ አስተዳደር በደብዳቤ ቁጥር አጣ/ከአስ/1952/2011 በቀን 18/08/2011ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የሚከተለውን ገልጧል፦

**ሀ. በአጣዬ ከተማ አስተዳደር መጋቢት 28 እና 29/2011 ዓ.ም በተፈጸመ ጥቃት የተገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር**

ሰንጠረዥ 2

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ቀበሌ |
|---|---|---|
| 1 | አቶ ተስፋ በቀለ | 03 |
| 2 | አቶ ዘዉዱ ተስፋዉ | 03 |
| 3 | አቶ ሁሴን እንድሪስ | 03 |
| 4 | አቶ እንዳለ መሸሻ | 02 |
| 5 | አቶ ስዩም ሀይሌ | 02 |
| 6 | አቶ አማረ መስያዉ | 02 |
| 7 | አቶወንደሰን አለማየሁ | 02 |
| 8 | አቶ ደበበ ይልማ | 03 |
| 9 | አቶ ዉብሸት አማረ | 01 |
| 10 | አቶ መተኪያ ናደዉ | 01 |
| 11 | አቶ ጋረደዉ ገብሬ | 02 |
| 12 | ወ/ሮ ዘነበች ጋሻዉ | 02 |
| 13 | ወ/ሮ አሚናት አሊ | 03 |
| 14 | ወጣት ሁሴን እንድሪስ | 01 |
| 15 | ወጣትአቡበከር ኡመር | 01 |
| 16 | አቶ አየለ አባተ | 01 |
| 17 | ወጣት አህመድ አደም | 01 |
| 18 | አቶ ንጉስ ወርቅሸት | 03 |
| 19 | አቶ በለጠ | 01 |

በአማራ ብ/ክ/መንግስት ጤና ቢሮ በሰሜን ሸዋ ዞን መስተዳድር ጤና መምሪያ የአጣዬ ዲስትሪክት ሆስፒታል በቁ.አጣጣዲ/ሆ/015/10594/11 በቀን 17/08/2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በግጭቱ ምክንያት ተጎድተው በሆስፒታሉ የታከሙ 40 ተጎጂዎች መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 29 ሰዎች ህክምና ተደርጎላቸው ወደየመኖሪያቸው መመለሳቸውን፣ 8 ሰዎች ለከፍተኛ ህክምና መላካቸውን እና ቀሪዎቹ 3 ሰዎች ህይወታቸው ያለፈ መሆኑን ደብዳቤው ያስረዳል፡፡ ህይወታቸው ያለፈው ሶስት ሰዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1) አቶ ቴዲ አሰፋ
2) አቶ በለጠው
3) ኮ/ል ታዲዮስ የተባሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

**ለ. ማጀቴ ከተማ ውስጥ መጋቢት 29 ቀን/2011 በሥራ ላይ እንዳሉ በታጣቂዎች በጥይት የተገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር** (ከኤፍራታና ግድም ወረዳ አስተዳደርና ከሟች ቤተሰቦች የተገኘ)

ሰንጠረዥ 3

| ተ.ቁ | የሟች ሙሉ ስም | ጾታ | ሥራ | ቀብሩ የተፈፀመበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ደበበ አየለ | ወ | ግብርና | ማጀቴ መድኃኒአለም ቤ/ክ |
| 2 | አቶ አሰፋ በረደድ | ወ | ግብርና | ማጀቴ መድኃኒአለም ቤ/ክ |
| 3 | አቶ ጌታቸው ስለሺ | ወ | ግብርና | ማጀቴ መድኃኒአለም ቤ/ክ |
| 4 | ኢንስፔ/ር ጌታቸው በየነ | ወ | ፖሊስ | ማጀቴ መድኃኒአለም ቤ/ክ |
| 5 | አቶ ካሳሁን ሞልቶት | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 6 | አቶ መኮንን የምሩ | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 7 | አቶ ቦጋለ ውብሸት | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 8 | አቶ የቻለ ይገዙ | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 9 | አቶ ተሰማ ጌታነህ | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 10 | አቶ እንግዳሰው አስፋው | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 11 | አቶ አድነው እሸቴ | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 12 | አቶ ደምሰው ምትኬ | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 13 | አቶ አየለ ሻረው | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 14 | አቶ አበበ ሹመቴ | ወ | ግብርና | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 15 | ሳጅን ዮሐንስ ተስፋዬ | ወ | ፖሊስ | ማጀቴ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 16 | አቶ አስዋብእስማኤል | ወ | ግብርና | የሙስሊም መቃብር፣ አጃፈጅ ቀበሌ |
| 17 | አቶ ሽጋውታደሰ | ወ | ግብርና | ስላሴ ቤ/ክ ገተም ቀበሌ |
| 18 | አቶ ተፈራበየነ | ወ | ግብርና | ስላሴ ቤ/ን ገተም ቀበሌ |
| 19 | አቶ ሁሴንአህመድ | ወ | ግብርና | የእስልምና መቃብር፣ መስኖ ቀበሌ |
| 20 | አቶ ካሳበለጠ | ወ | ግብርና | ውጂብ የሙስሊም መቃብር ቀበሌ |
| 21 | አቶ ጌታቸውታደሰ | ወ | የቀንሰራተኛ | መድሃኒአለም ቤ/ክ ማጀቴ |

**ሐ. ካራቆሪና ቆሪ ሜዳ መጋቢት 29 ቀን 2011 ዓ.ም በታጣቂዎች በጥይት የተገደሉ ሰዎች ስም ዝርዝር** (ሁሉም ሟቾች ሆስፒታል ሳይደርሱ ዐርፈዋል፤ መረጃው ከኤፍራታና ግድም ወረዳ አስተዳደርና ከሟቾች ቤተሰቦች የተገኘ ነው)

ሰንጠረዥ4

| ተ.ቁ. | ሙሉ ስም | ጾታ | ሥራ | የተቀበሩበት ሥፍራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ምንዳዬ ማርዬ | ወ | ግብርና | ካራቆሬ ሚካኤል |
| 2 | አቶ አያሌው መኮንን | ወ | ግብርና | ካራቆሬ ሚካኤል ቤ/ክ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | አቶ ምንዳዬ መኮንን | ወ | ግብርና | ካራቆሬ ሚካኤል ቤ/ክ |
| 4 | አቶ ላቀው ሺፈራው | ወ | አናጢ | ሰለሎ ሚካኤል ሰለሎ ቀ/ገ/ማ |
| 5 | አቶ ሻረው ታደሰ | ወ | ግብርና | ቆሪሜዳ ሚካኤል ቤ/ክ |
| 6 | አቶ ሙላት ተፈራ | ወ | ሾፌር | ካራቆሬ ሚካኤል ቤ/ክ |
| 7 | የአስር አለቃ ንጉሴ አሸኔ | ወ | ጡረተኛ | ካራቆሬ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 8 | አቶ ሀይለጊዮርጊስ መኮንን | ወ | ዲያቆን | ካራቆሬ ሚካኤል ቤ/ክ |
| 9 | አቶ በለጠው መሸሻ | ወ | ግብርና | መድሃኒአለም ቤ/ክ ካራለጎማ ቀበሌ |
| 10 | ወ/ት አየለች ቸርነት | ሴ | ግብርና | ኪዳነምህርት ቤ/ክ ብርብራ ቀበሌ ገ/ማ |
| 11 | አቶ ሹመት ደጉ | ወ | በያጅ | ሰለሎ ሚካኤል ሰለሎ ቀበሌ ገበሬ ማህበር |
| 12 | አቶ አማረ ግዛው | ወ | ጥበቃ | ቆሪሜዳ ሚካኤል ቤ/ክ |
| 13 | አቶ ካሳው ፋንታ | ወ | ግብርና | ኪዳነምህረት ቤ/ን ብርብራ ቀበሌ ገበሬ ማህበር |
| 14 | ኮንስታብል ታዲዮስ ደርሶ | ወ | ፖሊስ | ሰሜን ጎንደር |
| 15 | አቶ ንጉሴ ሸኔ | ወ | ነጋዴ | ቆሪሜዳ ገብርኤል ቤ/ክ |
| 16 | አቶ በለጠው ደጉ | ወ | ግብርና | መድሃኒአለም ቤ/ክ ካራለጎማ |
| 17 | አያልነሽ ጌታቸው | ሴ | ነጋዴ | ብርብራ ኪዳነምህርት ቤ/ክ ቆሪሜዳ |

**በአማራ ብ/ክ/መ/የኦሮሞ ብሔር አስተዳደር ዞን የተገኘ ሰነድ እንደሚያስረዳው ከ28/07/2011-30/07/2011ዓ.ም በአጣዬ ከተማ እና አካባቢዋ በተፈጠረ ግጭት ህይወታቸውን ያጡ የጂሌ ጥሙጋ ወረዳና አርጡማ ፉርሲና አካባቢው ነዋሪዎች ስም ዝርዝር**

**ሰንጠረዥ5**

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | እድሜ | ቀበሌ | ቀን | የተመታበትቦታ | ከተማ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አህመድ አልይአበጋር | 29 | ዱላ | 28/07/2011 | ደረቱን | አጣዬ |
| 2 | ኡመር ሂንሴ | 55 | ዱላ | 29/07/2011 | ጭንቅላቱን | ኢዝግዬ |
| 3 | አሊሚራ ኡመርሂንሴ | 43 | ዱላ | 29/07/2011 | ሆዱን | ኢዝግዬ |
| 4 | ዘየኑ አደም | 55 | ዱላ | 30/07/2011 | ጭንቅላቱን | ኢዝግዬ |
| 5 | አወል አብደላ | 38 | ዱላ | 30/07/2011 | አፉን | ኢዝግዬ |
| 6 | ሀሰን አብደላ አደም | 47 | ወረሌንጫ | 29/07/2011 | ጭንቅላቱን | አጣዬ |
| 7 | አህመድ ኡመር የሱፍ | 33 | መታሆራ | 29/07/2011 | ዓይኑን | አጣዬ |
| 8 | ኡመር አህመድ ዱኮ | 31 | ያቱመረር | 29/07/2011 | እንብርቱ ላይ | አጣዬ |
| 9 | ቀንዲሉ መሐመድ | 47 | አርቦዋዩ | 29/07/2011 | ደረቱን | አጣዬ |
| 10 | አህምያ አደም አረቡ | 33 | አርቦዋዩ | 29/07/2011 | ሆዱን | አጣዬ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | አወል ኡመር እንድሪስ | 9ወር | አርቦዋዩ | 29/07/2011 | የጎንሆዱን | አጣዬ |
| 12 | መሀመድ በሽር ከማል | 31 | ካሮጰ | 27/07/2011 | ደረቱን | ደዌ |
| 13 | ሁሴን መሀመድ ሁሴን | 34 | አረኔ | 27/07/2011 | ጭንቅላቱን | ደዌ |
| 14 | ኡስማን ቡርካን | 42 | ጨፋ2 | 27/07/2011 | ደረቱን | ጨፋ |
| 15 | መሀመድ አህመዴ | 37 | ጫካ | 27/07/2011 | ደረቱን | ጨፋ |
| 16 | አህመድ አሩሶ | 36 | ፋቲ | 27/07/2011 | ደረቱን | ጨፋ |
| 17 | ጀማል ሀሸም | 45 | ደሬንሳ | 28/07/2011 | ሆዱን | ጨፋ |
| 18 | ሀሰን አማሪ | 60 | ጃራ | 28/07/2011 | ደረቱን | ጨፋ |
| 19 | አብዲ ኡመር ግዘዮ | 43 | ጭረቲዲሬ | 28/08/2011 | ዓይኑን | ጨፋ |

### 4.2.3. አካል ጉዳት

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 16 ‹‹ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው›› ሲል ይደነግጋል፡፡ የሰዎች የአካል ደኅንነት የመጠበቅ መብት የማይደፈርና የማይገሠሥ መሆኑን የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 14 ያረጋግጣል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌን መንግስት ባለማስከበሩ ምክንያት በሚከተሉት ግለሰቦች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

**በአጣዬ ከተማ በመጋቢት 28 እና 29/2011 ዓ.ም በተከሰተው ግጭት የቆሰሉ ዜጎች ዝርዝር** (ከአጣዬ ከተማ አስተዳደር የተገኘ)

**ሰንጠረዥ 6፡**

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ቀበሌ | የደረሰበት ጉዳት |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ጀማል አደም | 01 | ከባድ ቁስለት |
| 2 | የ፲ አለቃ ግርማ | 01 | ከባድ ቁስለት |
| 3 | አቶ ስሶ ጫኔ | 01 | ከባድ ቁስለት |
| 4 | አቶ ሻንበል ጠጂ | 01 | ከባድ ቁስለት |
| 5 | አቶ አሊ ኡመር | 01 | ከባድ ቁስለት |
| 6 | አቶ አህመድ ሰይድ | 01 | ከባድ ቁስለት |
| 7 | አቶ አብዱዬ አህመድ | 01 | ከባድ ቁስለት |
| 8 | አቶ ኡስማን | 01 | ከባድ ቁስለት |
| 9 | አቶ እሸቱ በላይ | 02 | ከባድ ቁስለት |
| 10 | አቶ አሜ ሁሴን | 02 | ከባድ ቁስለት |
| 11 | አቶ ደረሰ ሺበሺ | 02 | መካከለኛ ቁስለት |
| 12 | አቶ ወልዴ በላይ | 02 | መካከለኛቁስለት |
| 13 | አቶ ሁሴን አህሜ | 02 | ቀላል ቁስለት |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 14 | አቶ ሳሙኤል አበራ | 03 | መካከለኛ ቁስለት |
| 15 | ወ/ሮ ጉመይ አደፍርስ | 03 | ከባድቁስለት |
| 16 | ቢኒያም ኑርአየሁ | 03 | ከባድ ቁስለት |
| 17 | አቶ ደምሰዉ ስለ | 03 | ቀላል ቁስለት |
| 18 | አቶ ንጉስ ደስታ | 03 | መካከለኛ ቁስለት |
| 19 | አቶ አህመድ ሰይድ | 03 | ቀላል ቁስለት |
| 20 | 10 አለቃ ቢልልኝ | 02 | ከባድ ቁስለት |

**መጋቢት 29 ቀን 2011 ዓ.ም በማጀቴ ከተማ በታጣቂዎች በተፈፀመጥቃትበጥይት የቆሰሉ** (ከኤፍራታና ግድም ወረዳ አስተዳደርና ከተጎጂዎች ቤተሰቦች የተገኘ)

**ሰንጠረዥ 7፡**

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ፆታ | ሥራ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ምናለ ወርቅሸት | ወ | ግብርና |
| 2 | አቶ ፈለቀ ሙላቱ | ወ | ግብርና |
| 3 | አቶ ቶማስ በለጠው | ወ | የቀን ሠራተኛ |
| 4 | አቶ ዘመድኩን አየለ | ወ | ግብርና |
| 5 | አቶ አየለ ጌታነህ | ወ | ግብርና |
| 6 | አቶ ሙላቱ ከበደ | ወ | ግብርና |
| 7 | አቶ አስረስ ጸጋው | ወ | ግብርና |
| 8 | አቶ ይማም ገሰጠው | ወ | ግብርና |
| 9 | አቶ ደስታ ግዛው | ወ | ግብርና |
| 10 | አቶ ግርማ ፈረደኝ | ወ | ግብርና |
| 11 | አቶ ዘነበ ግዛው | ወ | ግብርና |
| 12 | አቶ ደምሰው ገበየሁ | ወ | ግብርና |
| 13 | አቶ በቀለ ግዛው | ወ | ግብርና |
| 14 | አቶ ወርቅሸት አወቀ | ወ | ግብርና |
| 15 | አቶ አጥላው ጌታቸው | ወ | ግብርና |
| 16 | አቶ ሙሃባ መሀመድ | ወ | ግብርና |
| 17 | አቶ በቀለ ይርጋ | ወ | ግብርና |
| 18 | አቶ ደረሴ አበበ | ወ | ግብርና |
| 19 | አቶ አጥላው ድረሴ | ወ | ግብርና |
| 20 | አቶ ጌጠነህ አያሌው | ወ | ግብርና |
| 21 | አቶ ደምስ ግዛው | ወ | ግብርና |
| 22 | ወጣት ረታ ደጀኔ | ወ | ግብርና |
| 23 | ወጣት ሻምበል ትርፌ | ወ | ተማሪ |

**ካራቆሬ/ቆሪ ሜዳ ከተማ መጋቢት 29 ቀን/2011 ዓ.ም በታጣቂዎች በተተኮሰ ጥይት የቆሰሉ (ከኤፍራታና ግድም ወረዳ አስተዳደርና ከተጎጂዎች ቤተሰቦች የተገኘ)**

**ሰንጠረዥ 8**

| ተ.ቁ | ሙሉ ሥም | ጾታ | ሥራ |
|---|---|---|---|
| 1 | አቶ አበበ በላይነህ | ወ | አርሶአደር |
| 2 | አቶ በቀለ ንጉሴ | ወ | አርሶአደር |
| 3 | አቶ አልታዬ ንጉሴ | ወ | ጥበቃ |
| 4 | አቶ ገለታው ደበበ | ወ | አርሶአደር |
| 5 | አቶ ሻምበል ተፈራ | ወ | አርሶአደር |
| 6 | አቶ ጥላሁን በላቸው | ወ | አርሶአደር |

**በአማራ ብ/ክ/መንግስት በኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን በጂሌ ጥሙጋ፣ አርጡማ ፉርሲና አካባቢው ባሉ ወረዳ ነዋሪዎች ከ28/07/2011-30/07/2011 በአጣዬ ከተማና አከባቢዋ በተፈጠረው ግጭት በጥይት የቆሰሉ (ከኦሮሞ ብሔረሰብ ልዩ ዞን አስተዳደር የተገኘ)**

**ሰንጠረዥ 9**

| ተ.ቁ | ሙሉ ስም | ዕድሜ | ቀበሌ | የተመታበት ቀን | የተመታበት ቦታ | የተመታዉ አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ማሞ ሀሰን ቱካ | 31 | ያቱ መረር | 28/07/2011 | አጣዬ | ክንዱን |
| 2 | መሀመድ ሀሰን አብደላ | 42 | መርማ ሀደሬ | 28/07/2011 | አጣዬ | ክዱንና እግሩን |
| 3 | ኡስማን አህመድ አል | 36 | መተሆራ | 28/07/2011 | አጣዬ | ቀኝ እጁን |
| 4 | ኡመር አሜ መሀመድ | 30 | ሰንበቴ | 28/07/2011 | አጣዬ | መሀል አንገቱን |
| 5 | መሀመድ አህመድ | 31 | ወረሌንጫ | 29/07/2011 | አጣዬ | ቀኝ እግር |
| 6 | መሀመድ አልይ ይ | 32 | ፉኛን ደንዲ | 29/07/2011 | አጣዬ | ቀኝ እግር |
| 7 | አሜ መሀመድ | 66 | እዝግዬ | 29/07/2011 | እዝግዬ | ደረቱ ላይ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 8 | ሁሴን አሜ | 27 | እዝግዬ | 29/07/2011 | እዝግዬ | ቀኝ እጁን |
| 9 | ኑራ አህመድ አመር | 32 | ጋነገሃ | 29/07/2011 | አጣዬ | ግራ እግሩን |
| 10 | ኡመር አሚ ኡመር | 38 | ገርቢ ድሬ | 29/07/2011 | አጣዬ | ቀኝ እግሩን |
| 11 | ኡስማን ሀሰን | 45 | አርበዋዩ | 28/07/2011 | አጣዬ | ግራ እግር |
| 12 | አህመያ ሰይድ ሁሴን | 46 | አርበዋዩ | 28/07/2011 | አጣዬ | ትክሻዉን |
| 13 | አህመድ ሁሴን ዳይድ | 31 | አርበዋዩ | 29/08/2011 | አጣዬ | ራሱን |
| 14 | ቡሽራ መሀመድ | 33 | አርበዋዩ | 29/07/2011 | አጣዬ | ትክሻ |
| 15 | አብዱ አህመድ | 10 | አርበዋዩ | 29/07/2011 | አጣዬ | ታፋዉን |
| 16 | አህመድ ኡመር | 34 | ያቱ መረር | 29/07/2011 | አጣዬ | እግሩ ተቆርጧል |
| 17 | አዳሜ አህመድ | 38 | ጭ/ኦ | 27/08/2011 | ጨፋ | ቀኝእግር |
| 18 | አህመድ ዊሎ | 34 | ቀጨማ | 27/07/2011 | ጨፋ | ትክሻ |
| 19 | አደም ኡመር | 42 | ፉርሲ ማርጡ | 27/07/2011 | ጨፋ | እጁን |
| 20 | ጣሂር አሊሻ | 34 | ፋቲ | 27/07/2011 | ጨፋ | ቀኝ እግሩን |
| 21 | ሁሴን ኡመር | 45 | ፋቲ | 27/07/2011 | ጨፋ | እራሱን |
| 22 | መሀመድ አህመድ | 29 | መርማ አልዩ | 27/07/2011 | ጨፋ | ቀን እጁን |
| 23 | መሀመድ አህመድ | 37 | ዋ ቦሩ | 27/07/2011 | ጨፋ | ደረቱን |
| 24 | ሁሴን አህመዴ | 35 | ጭረቲ | 27/07/2011 | ጨፋ | እግሩን |
| 25 | ኡመር ማማ | 45 | ሙጤ | 27/07/2011 | ጨፋ | ግራ እግሩን |
| 26 | አህመድ ሁሴን | 42 | ራሳ | 27/07/2011 | ጨፋ | ቀኝ እግር |
| 27 | አህመድ አልይ | 47 | ዶቢ | 27/07/2011 | ጨፋ | ትክሻ |
| 28 | መሀመድ አልይ | 38 | አኩርፎ | 27/07/2011 | ጨፋ | እጁን |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 29 | አህመድ መሀመድ | 37 | ራሳ | 27/07/2011 | ጨፋ | ቀኝ እግሩን |
| 30 | አህመድ ሀሰን | 47 | ራሳ | 27/07/2011 | ጨፋ | እራሱን |
| 31 | መሀመድ ሁሴን | 38 | ራሳ | 27/07/2011 | ጨፋ | ቀኝ እጁን |
| 32 | መሀመድ አህሙ | 51 | ጭረቲ | 27/07/2011 | ጨፋ | ደረቱን |
| 33 | ሁሴን አህመድ | 36 | ወደደር | 27/07/2011 | ጨፋ | ትክሻ |
| 34 | አሾ ጎጀቤ | 33 | ጭረቲ2 | 27/07/2011 | ጨፋ | እጁን |
| 35 | ሲራጅ ሁሴን | 34 | ጭረቲ2 | 27/07/2011 | ጨፋ | ቀኝ እግሩን |
| 36 | አህመድ ሰይድ | 33 | ጨረቲ2 | 27;07/2011 | ጨፋ | እራሱን |
| 37 | አህመድ ሰይድ ሁሴን | 31 | ቱሉ ቀጨማ | 27/07/2011 | ጨፋ | ቀኝ አጁን |

### 4.2.4. ማፈናቀል

በኤፍራታና ግድም ወረዳ በተለያዩ ቀበሌዎች በተፈፀመው ጥቃት ምክንያት ከቤት ንብረታቸው 3,730 የሚሆኑ አባወራዎች፣ በቤተሰብ ደረጃ 9,325 ዜጎች መፈናቀላቸውንና በንብረት ላይ የደረሰውን ጉዳት መረጃ የማሰባሰብ ስራ እየተሰራ መሆኑን ኤፍራታና ግድም ወረዳ አስተዳደር ፅ/ቤት በቁጥር ኤ/ግ/ወ/አስ 3202/11 በ15/08/2011 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ገልፆልናል፡፡

ይህ ሪፖርት እየተጠናቀረ ባለበት ወቅት ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው መመለሳቸውንና ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ግለሰቦች እርዳታ እንደተደረገላቸው ኢሰመጉ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

**ናሙና ፎቶግራፎች**

**የተገደሉ ሰዎች ፎቶ ግራፎች በጥቂቱ (በአጣየ፣ ማጀቴና ካራቆሪ አካባቢ የተገደሉ)**


ኢንስፔክተር ጌታቸው


ዋ/ሳጅን ዮሀንስ


አበበ አየለ



አማረ ግዛው



ጋርደው ገብሬ



ሻምበል ጋሻው



ሙላቱ ተፈራ



ምንዳዮ ማርየ



ሹመት ደጉ



ካሳው ፈንታ



ላቀው ሽፈራ



ወንደሰን አለማየሁ



አያሌው መኮንን



ምንዳየ መኮንን



አያልነሽ ቸርነት



ደበበ አየለ



ኡስማን መሀመድ



ሻረው ታደሰ



አማረ ማከያው

**በጥይት የቆሰሉ ሰዎች ፎቶግራፍ**



ገለታው ደበበ



ጀማል አደም



ሻምበል ተፈራ



ኮከቤ ንጉሴ



ቶማስ በለጠ

### 4.2.5. ጉዳዩ አሁን የሚገኝበት ሁኔታ

ጥቃት በተፈፀሙባቸው እና ግጭቶች በተፈጠሩባቸው የሰሜን ሸዋ ዞን አካባቢዎች የመከላከያ ሠራዊትና የአማራ ክልል ልዩ ኃይል ከተሰማሩ በኋላ አሁን ያለው ሁኔታ የተረጋጋ ነው፡፡ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ወደ ቀድሞው መኖሪያ ቤታቸው ተመልሰዋል፡፡ ይሁንና አሁንም ድረስ በኅብረተሰቡ አኳያ ሥጋት እንዳለ የአካባቢው ነዋሪዎች ለኢሰመጉ ገልፀዋል፡፡ ይህ ሪፖርት በተጠናቀረበት ወቅት የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ የኃይማኖት መሪዎችና የሀገር ሽማግሌዎች ጥረት ማድረጋቸውን እና በድርጊቱ የተጠረጠሩ በርካታ ግለሰቦች ተይዘው ለሕግ የቀረቡ መሆኑን ኢሰመጉ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

## 4.3. በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ማንዱራ ወረዳ የተፈፀሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 15 በሕይወት የመኖር መሠረታዊ መብትን ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም ይህ መብት የማይደፈርና የማይገሠሥ መሆኑን የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 14 ይደነግጋል፡፡ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 32 (1) ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት፣ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነጻነት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችውና ፍጹም አስገዳጅ የሆነው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳንም በአንቀጽ 6 ንዑሥ አንቀጽ 9 ላይ እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር ተፈጥሯዊ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ሕገ መንግሥታዊና ዓለም አቀፋዊ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች በመተላለፍ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ተፈጽመዋል፡፡

መስከረም 16 ቀን 2011 ዓ.ም የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማሼ ዞን አመራሮች ከምእራብ ኦሮሚያ አስተዳደር ጥምር ኮሚቴ ጋር የነበራቸውን ስብሰባ አጠናቅቀው ሲመለሱ ምዕራብ ወለጋ ዞን ቢላ ወረዳ ላይ ማንነታቸው ባልታወቀ ታጣቂዎች በተሰነዘረባቸው ጥቃት 4 አመራሮች በመገደላቸው

ለግጭት መቀስቀስ ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህን ግድያ ተከትሎ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማሼ ዞን በሎይ ጅጋንፎ ወረዳ ዳለቻና ታንኮና በተባሉ ቀበሌዎች በዋናነት ግጭት ተፈጥሯል፡፡

ኢሰመጉ እስካሁን ባሰባሰበው መረጃ ለማረጋገጥ እንደቻለው ከግጭቱ ጋር በተያያዘ ከ90,000 (ዘጠና ሺ) በላይ የሚሆኑ ሰዎች ቤት ንብረታቸውን ጥለው ወደ አጎራባች አካባቢዎች ተሰድደዋል፣ ከ200 በላይ ቤቶች ተቃጥለዋል፣ ከ74 በላይ የሰው ሕይወት ጠፍቷል እንዲሁም በርካቶች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

ተፈናቃዮች ለወራት በነቀምትና በተለያዩ ከተሞች ተጠልለው እርዳታ ሲደረግላቸው ቆይተው በሁለቱ የክልል አመራሮች መካከል በተደረገው ስምምነት መሰረት ወደ ቀያቸው እንዲመለሱ የተደረገ ቢሆንም ለተቃጠሉ ቤቶች መጠለያ ባለመሠራቱና ከቃጠሎ በተረፉት ቤቶች ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ፈጻሚዎቹ በኃይል ገብተው እየኖሩ በመሆናቸው ተመላሾቹ በመንግስት ተቋማት እንዲጠለሉ ተገደዋል፡፡ በዚህ ድርጊት እጃቸው ያለበት ሰዎች በሕግ አለመጠየቃቸውና እንዲሁም በተመላሾች ላይ ዛቻና ማስፈራሪያ በመፈጸሙ ምክንያት ቁጥራቸው 198 የሚሆኑ አባወራዎች በስጋት ወደ ኦሮሚያ ክልል ጊዳ አያና ወረዳ በዴሳ ቀበሌ ተመልሰው በመጠለያ ድንኳን ውስጥ እንደሚገኙ በቀን 18/11/2011 ዓ.ም ለኢሰመጉ በጻፉት ማመልከቻ አሳውቀዋል፡፡ እየቀረበላቸው ያለው ሰብዓዊ እርዳታና ድጋፍ በቂ እንዳልሆነ የገለጹት ተፈናቃዮች ሰላም ለማስፈን በሥፍራው ተሠማርቶ የነበረው የመከላከያ ሠራዊት አካባቢውን ለቅቆ እንዲወጣ በመደረጉ ሥጋት ላይ መውደቃቸውን አስታውቀዋል፡፡

በተጨማሪም፣ በአካል ቀርበው ለኢሰመጉ አቤቱታ ያቀረቡ የተፈናቃዮች ተወካዮች እንዳስረዱት ስለደረሰባቸው ጉዳት ምንም ነገር መናገርም ሆነ መጠየቅ እንደማይችሉ፣ ስለሞቱባቸው ሰዎች ምንም ዓይነት ጥያቄ እንዳያቀርቡ (‹‹አስከሬን እንቀብራለን››፣ ‹‹እናነሳለን›› የሚል ጥያቄንም ያካትታል)፣ ስለ ደረሰባቸው ጉዳት እንዳይናገሩም ሆነ ጉዳት ያደረሱባቸውን ሰዎች ስም እንዳይጠቅሱ፣ ስለ ንብረታቸውም እንዳይጠይቁ የኦሮሚያና የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልሎች ባለ ሥልጣናት በጋራ ማስጠንቀቂያ ሰጥተዋቸዋል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሰለባዎቹ አሁን የሚገኙበትን ሁኔታ ለማጣራት ኢሰመጉ ባደረገው ሙከራ በተፈጸመባቸው ጥቃት የተነሣ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው የነበሩ ዜጎች መጠለያ ስላልተሠራላቸው በጊዜአዊነት በሌሎች ሰዎች ዘንድ ተጠግተው እየኖሩ ነበር ዕርዳታ የሚቀበሉት፤ ወደ ቀድሞ ቀዬአቸው ተመልሰው ቤት ሠርተው ካልገቡ ዕርዳታ እንዳያገኙ ክልከላ ይደረግባቸው ነበረ፡፡ ይህ ሪፖርት በተጠናቀረበት ወቅት ወደ ቀያቸው ተመልሰዋል፡፡

## 4.4. በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ሲዳማ ዞን የተለያዩ አካባቢዎች ውስጥ የተፈጸሙ የተለያዩ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች

ሰንጠረዥ 1፡ በዚህ ምርመራ የተሸፈኑ ወረዳዎች

| ተ.ቁ | ዞን | ወረዳ | ቀበሌ |
|---|---|---|---|
| 1 | ሲዳማ | ሸበዲኖ | |
| 2 | ›› | ማልጋ | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 3 | ›› | ይርጋለም | |
| 4 | ›› | ሀዋሳ ከተማና ዙሪያ | |
| 5 | ›› | አለታ ወንዶ ከተማ | |
| 6 | ›› | አርቤጎና | |
| 7 | ›› | ዳሌ | |
| 8 | ›› | ሁላ | |
| 9 | ›› | ወንዶ ገነት | |
| 10 | ›› | አለታ ጩኮ | |
| 11 | ›› | ጭሮኔ | |

#### 4.4.1. መግቢያ

ይህ የመግለጫው ክፍል የሚሸፍነው ሐምሌ 11 እና 12 ቀን 2011 ዓ.ም በሲዳማ ዞን ልዩ ልዩ ወረዳዎች የተፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ የምርመራ ባለሙያዎቹን ከላይ ወደ ተጠቀሱት ወረዳዎች በማሠማራት የመስክ ምርመራ አከናውኗል፡፡ ከሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሠለባዎችና ከተጎጂዎች ቤተሰቦች ጋር ቃለ መጠይቅ አድርጓል፣ ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትም የደረሰውን ጉዳት ዝርዝር የሚያሳዩ ሠነዶችን አሰባስቧል፡፡

ኢሰመጉ ባከናወነው ምርመራ ለማረጋገጥ እንደተቻለው ከሲዳማ የክልልነት ጥያቄ ጋር ተያይዞ ‹‹ኤጄቶ›› በሚል ሥያሜ ተሰባስበው የሚንቀሳቀሱ ወጣቶች በዞኑ ነዋሪዎች በሆኑ የሌሎች ብሔሮች ተወላጆች ላይ በፈጸሚቸው ጥቃቶችና ይህን ተከትሎ ሁከቱን ለማስቆም በዞኑ የተሠማራው የመከላከያ ሠራዊት በወሰደው ርምጃ በሁለቱ ቀናት 49 ሰዎች ተገድለዋል፣ 36 ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ግምቱ 334 ሚሊዮን 903 ሺህ 592 ብር የሆነ ንብረት ወድሟል፡፡

በሲዳማ ዞን በተለያዩ ወረዳዎች የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን አስመልክቶ በኢሰመጉ የሀዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት አማካይነት ማስረጃ ሲሰባሰብ ቆይቷል፡፡ የቀጠናው ጽ/ቤት ባለሙያዎች ከተጎጂዎችና ከምስክሮች ጋር በየጊዜው እየተገናኙ ቃል ሲቀበሉ፣ ማስረጃ ሲያሰባስቡና በየሳምንቱም በአካባቢው ስለነበረው ሁኔታ ለዋና ጽ/ቤት ሲያስታውቁ ቆይተዋል፡፡ በየጊዜው የተሰበሰበውን መረጃና ማስረጃ እውነተኛነት ለማጣራትና ለማረጋገጥ ልዩ ጥንቃቄ ተወስዶ በመስክ ምርመራ ጭምር የተደገፈ ሥራ ተከናውኗል፡፡ ኢሰመጉ የመረጃና ማስረጃ ምንጮቹን ማንነት በምሥጢር ለመጠበቅ ተገቢውን የጥንቃቄ ርምጃ ወስዷል፡፡

#### 4.4.2. የችግሩ የኋላ ታሪክ

ከሲዳማ የክልልነት ጥያቄ ጋር በተያያዘ በተለያዩ ጊዜያት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ሲፈጸሙ ቆይተዋል፡፡ ግንቦት 16 ቀን 1994ዓ.ም ‹‹የሲዳማ ክልል የመሆን ሕገ መንግሥታዊ መብቱ ይጠበቅለት›› የሚል መፈክር አንግበው በእጃቸው ከእንሰት ዝንጣፊና እርጥብ ሣር በቀር የጦር መሣሪያ ሳይዙ ጥያቄአቸውን ለመንግሥት ለማቅረብ በሞከሩ ሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ የመንግሥት ኃይሎች ከመኪና ላይ በተጠመደ መትረየስ ተኩስ በመክፈት 25 ሰዎችን ገድለዋል፤ በብዙዎች ላይም የአካል ጉዳት አድርሰዋል፡፡ ይህንንም አስመልክቶ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ ‹‹በሀዋሳና አካባቢው

በሚገኙ ነዋሪዎች ላይ የደረሰ አስከፊ የመብት ረገጣ›› በሚል አርእስት ግንቦት 21 ቀን 1994ዓ.ም ባወጣው 51ኛ ልዩ መግለጫው ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ይፋ አድርጓል፡፡

የሲዳማ ሕዝብ በክልል በመደራጀት የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን ሕገ መንግሥታዊ መብቱ እንዲከበርለት ላነሣው ጥያቄ የኢሕአዴግ መንግሥት ተገቢውን ሕጋዊ ምላሽ በወቅቱ ሳይሰጥ በመቅረቱ በሰላማዊ መልክ ተጀምሮ የነበረው የሕዝብ ጥያቄ ወደ ሕዝባዊ እምቢተኛነትና ዐመጽ እንዲለወጥ ምክንያት ሆኗል፡፡ በተለይም በ2010 ዓ.ም በአገሪቱ የመጣውን ፖለቲካዊ ለውጥ ተከትሎ ጥያቄው ኃይልን በመጠቀም ጭምር ሲቀርብ ተስተውሏል፡፡

ከዚሁም ጋር በተያያዘ ከሰኔ 5 ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ በሀዋሳ ከተማና ዙሪያዋ በተፈጸመ ጥቃት ምክንያት በሲዳማ ዞን የሚኖሩ የሌሎች ብሔሮች ተወላጆች ግድያ ተፈጽሞባቸዋል፣ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ ሀብት ንብረታቸው ወድሞባቸዋል፣ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል፡፡ ኢሰመጉ ታኅሣሥ 11 ቀን 2011ዓ.ም ባወጣው 146ኛ ልዩ መግለጫ የደረሰውን ጉዳት በዝርዝር ይፋ አድርጓል፡፡

የሲዳማ ሕዝብ በዞኑ ምክር ቤት አማካይነት ጥያቄውን ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ምክር ቤት አቅርቦ ጉዳዩም ተቀባይነት አግኝቶ ለፌዴሬሽን ም/ቤት ቀርቦ የፌዴሬሽን ም/ቤትም ጉዳዩን ተመልክቶ ሕዝበ ውሳኔ እንዲደረግ ወስኗል፡፡ ሆኖም ግን ምርጫ ቦርድ በፌዴሬሽን ም/ቤት ውሳኔ መሠረት በዞኑ ሕዝበ ውሳኔ ለማድረግ ወስኖ በመንቀሳቀስ ላይ እንዳለ ሐምሌ 11 ቀን 2011ዓ.ም በሁሉም የሲዳማ ዞን ወረዳዎችና በሀዋሳ ከተማ ‹‹በ11/11/11 የሲዳማ ክልልነት መታወጅ አለበት›› የሚል መፈክር የሚያሰሙ ወጣቶች የተቃውሞ ሰልፍ አድርገዋል፡፡ በዕለቱ የተካሄደው ሰልፍ ወደ ዐመጽ በመለወጡ ብሔር የለየ ግድያ በበርካታ ዜች ላይ ተፈጽሟል፣ በርካታ ሰዎች የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፣ የንግድና የመኖሪያ ቤቶች እንዲሁም የመንግሥት ተቋማት ተዘርፈዋል፣ ተቃጥለዋል፣ የእምነት ተቋማት ላይም ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል፡፡

የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶቹን የፈጸሙት ‹‹ኤጀቶ›› በሚባል ሥያሜ የተሰባሰቡ ወጣቶች ሲሆኑ፣ ሕግና ሥርዓት ማስፈጸም ይገባቸው የነበሩ የዞኑ የጸጥታ ኃይሎችም በድርጊቱ ላይ ተሳትፈዋል፡፡ አካባቢው በአሁኑ ሰዓት በወታደራዊ እዝ ሥር የሚገኝ ሲሆን፣ ኅዳር 10 ቀን 2012ዓ.ም በዞኑ ሕዝበ ውሳኔ ተካሂዶ በውጤቱም የሲዳማ የክልልነት ጥያቄ በአብላጫ ድምፅ የሕዝብ ድጋፍ አግኝቶ ጸድቋል፡፡

### 4.4.3. በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት (ሕገ ወጥ ግድያ)

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 3 እያንዳንዱ ሰው በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነቱ የመጠበቅ መብት እንዳለው ያረጋግጣል፡፡ ኢትዮጵያ ፈርማ የተቀበለችው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃልኪዳንም በአንቀጽ 6 (1) እና 9 (1) ላይ ይህንኑ መብት በማረጋገጥ፣ መንግሥታት በቃል ኪዳኑ የተረጋገጡትን መብቶች በግዛታቸው የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ እንዳለባቸውም በአንቀጽ 2(1) እና 2(2) ይደነግጋል፡፡ በአፍሪካ የሰዎችና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር አንቀጽ 4 ላይ ማንኛውም ግለሰብ በሕይወት የመኖር መብቱና የአካሉ ደኅንነት ሊከበርለትና ሊጠበቅለት እንደሚገባና እነዚህን መብቶቹን በዘፈቀደ ሊነፈግ እንደማይችል ተመላክቷል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 14 ‹‹ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደኅንነትና የነጻነት መብት አለው›› ሲል ይደነግጋል፡፡ በተመሳሳይ የኢፌዲሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 15 ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት እንዳለውና በሕግ ከተደነገገው ውጪ ሕይወቱን ሊያጣ እንደማይችል በግልጽ ደንግጓል፡፡ ኢትዮጵያም እነዚህን ዓለም አቀፍ እና

አሕጉራዊ የሰብዓዊ መብቶች ሠነዶች የተቀበለች ሐገር እንደመሆኗ ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር፣ የማስከበርና የማሟላት ግዴታ ተጥሎባታል፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህን ሕገ መንግሥታዊ፣ አሕጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ድንጋጌዎች መንግሥት ማስከበር ባለመቻሉ በሲዳማ ዞን በ11/11/2011ዓ.ም ‹‹ኤጀቶ›› በተባለ ሥያሜ የተሰባሰቡ ወጣቶች በፈጸሟቸው ብሔር ተኮር ጥቃቶች ምክንያትና ሁኔታውን ለማረጋጋት ወደ ሥፍራው በተሠማራ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በተወሰደ የኃይል ርምጃ በዜጎች ላይ በሕይወት የመኖር መብት ጥሰት ተፈጽሟል፡፡

ኢሰመጉ ባከናወነው የመስክ ምርመራ ለማረጋገጥ እንደቻለው ከ11/11/2011 ዓ.ም በፊት በነበሩት ቀናት የክልልነት ጥያቄው ከተከለከለ ‹‹የክልልነት ጥያቄውን ሊያስከለክሉ ይችላሉ›› በሚል ምክንያት ለጥቃት ዒላማ ተደርገው የተመረጡ ሰዎች ስም ዝርዝር ‹‹ኤጀቶ›› በሚባለው ቡድን ተበትኖ ነበር፡፡ በዝርዝሩ ውስጥ ስማቸው የተጠቀሰ ሰዎች ይህንን ጉዳይ ለወረዳ አመራሮች አስታውቀው የነበረ ቢሆንም ከሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት አስፈላጊው ጥበቃ ሳይደረግላቸው በመቅረቱ በዛቻው መሠረት ‹‹ኤጀቶ›› በተባለ ሥያሜ የተሰባሰቡ ወጣቶች በአሠቃቂ ሁኔታ ደብድበው እንደገደሏቸው የሟቾች ቤተሰቦች ለኢሰመጉ አመልክተዋል፡፡

በተለይም በሐገረ ሰላም ከተማ በ11/11/2011ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ከፍተኛ ድብደባ የተፈጸመባቸው ዜጎች ይታደጓቸው ዘንድ ለወረዳው አስተዳደርና የፖሊስ አካላት ‹‹የድረሱልኝ›› ጥሪ ቢያቀርቡም ማንም ሊደርስላቸው አልቻለም፡፡ ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች በማግሥቱ በ12/11/2011ዓ.ም በፖሊስ ታጅበው ወደ ሁላ ሆስፒታል ቢወሰዱም ቀደም ሲል ድብደባ የፈጸሙባቸው ወጣቶች የተኙበት ክፍል ድረስ በመግባት በዱላ፣ በእርጥብ ቀርከኻና በገጀራ የከፋ ጉዳት አድርሰውባቸው ገድለዋቸዋል፡፡

በዜጎች ላይ በአሠቃቂ ሁኔታ ግድያ ከመፈጸሙ በፊት ጥቆማ ደርሷቸው ምንም ዓይነት የመከላከል ርምጃ ለመውሰድ ፈቃደኞች ሳይሆኑ የቀሩ የወረዳ አስተዳደርና የፖሊስ ኃላፊዎች ይህ ሪፖርት እስከሚጠናቀርበት ጊዜ ድረስ ለሕግ ሳይቀርቡ በሥራቸው ላይ እንዳሉ ኢሰመጉ ባደረገው ምርመራ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 1 በሲዳማ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች ግድያ የተፈጸመባቸው ሰዎች ዝርዝር**

| ተ.ቁ | የተገደለው ሰው ስም | ዕድሜ | የተገደለበት ቀን | የተገደለበት ቦታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ገዛኸኝ ተስፋዬ | 42 | 12/11/2011 | ሁላ ሆስፒታል | |
| 2 | አዲሱ ገዛኸኝ | 17 | ›› | ›› | አባትና ልጅ ሲሆኑ በ‹‹ኤጀቶ›› ነው የተገደሉት |
| 3 | ግርማ መልካ | 84 | 11/11/11 | ሐገረ ሰላም | ›› |
| 4 | ሰለሞን ዘገየ | 26 | 12/11/11 | ›› | በመከላከያ ሠራዊት የተመታ |
| 5 | መኖ መልጌ | 30 | ›› | ›› | ›› |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ተስፋ ሄታሮ | 30 | ›› | ›› | ›› |
| 7 | ሰሎሞን ላንታ | 19 | ›› | ›› | ›› |
| 8 | ካቢሶ ከረዩ | 29 | ›› | ›› | ›› |
| 9 | ሳሙኤል ሙንጣሽ | 18 | ›› | ›› | ›› |
| 10 | ምትኩ ፋኖሌ | 28 | ›› | ›› | ›› |
| 11 | ዳርጌ ዮና | 40 | ›› | ›› | ›› |
| 12 | አርገታ አቶካ | 56 | ›› | ›› | ›› |
| 13 | ተሾመ አርጎ | | ›› | ›› | ›› |
| 14 | ለማ ላንቃሞ | 41 | ›› | ይርጋለም | ›› |
| 15 | ተሰማ አርጎ | 19 | 12/11/11 | ሐገረ ሰላም | በመከላከያ ሠራዊት የተመታ |
| 16 | ጅጉቴ ናሚቻ | 25 | ›› | ›› | ›› |
| 17 | ማሙሽ ተሰማ | 21 | ›› | ይርጋለም | ›› |
| 18 | ይስሐቅ ሁሬሳ | 16 | 11/11/11 | ሸበዲኖ ወረዳ | ›› |
| 19 | ተመስገን ሜጢ | 25 | 12/11/11 | ይርጋለም | ›› |
| 20 | ደከሞ ዲካ | 35 | 12/11/11 | ›› | ›› |
| 21 | ሙሴ ደስታ | 18 | 12/11/11 | ›› | ›› |
| 22 | መሪሁን ደግፌ | 10 | | ሸበዲኖ ወረዳ ለኩ 01 | ›› |
| 22 | ታምራት በላይ | 21 | | ለኩ 03 | ›› |
| 23 | የተራ ህርጳቶ | 42 | 11/11/11 | ማልጋ ወረዳ | ›› |
| 24 | ዋቆ አያሞ | 30 | ›› | ›› | ›› |
| 25 | ቦርቻ ቤካ | 40 | ›› | ›› | ›› |
| 26 | ሰንበቶ ባንቄ | 58 | | ›› | ›› |
| 27 | ቦና ቦኤ | 48 | ›› | ›› | ›› |
| 28 | ፋላቶ ቱሌ | 45 | ›› | ›› | ›› |
| 29 | ደቀማ ቦኤ | 47 | ›› | ›› | ›› |
| 30 | ተስፋዬ በቱካ | 50 | ›› | ›› | ›› |
| 31 | ከንባ ዋቀዩ | 40 | ›› | ›› | ›› |
| 32 | አቶ ባቶላ ዬዋ | 25 | ›› | ›› | ›› |
| 33 | ተስፋዬ ድንቶ | 28 | ›› | ›› | ›› |
| 34 | አቶ ካንታ ካቹላ | 40 | ›› | ›› | ›› |
| 35 | ኢያሱ ጋኖላ | 40 | ›› | ›› | ›› |
| 36 | አርጋው ቦኖራ | 45 | ›› | ›› | ›› |
| 37 | ባቂ ዱከሞ | 42 | ›› | ›› | ›› |
| 38 | ማቲዎስ ዲካሌ | 20 | ›› | ›› | ›› |
| 39 | እስቂል ያዕቆብ | 30 | ›› | ›› | ›› |
| 40 | ስሙ ያልታወቀ ሰው | 25 | ›› | ሐዋሳ ዙሪያ | ከአዳሬ ሆስፒታል በተገኘ ማስረጃ መሠረት |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ጭንቅላቱ ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ የሞተ |
| 41 | ሹምቡራ ዮቴ | 16 | 12/11/11 | ጎርቼ ወረዳ | ከአዳሬ ሆስፒታል በተገኘ ማስረጃ መሠረት ሆዱና ደረቱ ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ የሞተ |
| 42 | አረጋ ቡያ | 40 | ›› | ወንዶገነት | ከአዳሬ ሆስፒታል በተገኘ ማስረጃ መሠረት ሆዱ ላይ በጥይት ተመትቶ በሕክምና ሲረዳ ቆይቶ የሞተ |
| 43 | ወ/ሮ አመለወርቅ ፈቃደ | 45 | 11/04/2012 | | ‹‹ኤጀቶ›› በሚል ሥያሜ የተሰባሰቡ ወጣቶች ባደረሱባቸው ድብደባ ምክንያት ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በሕክምና ላይ ሳሉ ነው ያረፉት |
| 44 | ወ/ሪት ሰሚራ ቀልቤሳ | 17 | ›› | ቱላ | ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በተገኘ ማስረጃ መሠረት ሆዷ ላይ በጥይት ተመትታ የሞተች |
| 45 | ስሙ ያልታወቀ | 22 | ›› | - | ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በተገኘ ማስረጃ መሠረት በጥይት ተመትቶ የሞተ |
| 46 | ማርቆስ ዱባለ | 25 | ›› | - | ከሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በተገኘ ማስረጃ መሠረት ሆዱ ላይ በጥይት ተመትቶ የሞተ |
| 47 | መስፍን ብጡላ | 18 | 12/11/11 | | አገረሰላም |
| 48 | ዮሴፍ ቡቻቻ | 45 | ›› | | ›› |
| 49 | ይስሐቅ ሁሪሳ | 18 | 11/11/11 | ለኩ ከተማ | በመከላከያ ሠራዊት የተገደለ |

<u>የተገደሉ ሰዎች ፎቶ ግራፎች ናሙና</u>



አዲሱ ገዛኸኝ



አርገታ ኦቶካ



ዳርጌ ዮና



ገዛኸኝ ተስፋዬ



ግርማ መልካ



ጅግቴ ናኤቻ



ካቢሶ ከረዩ



ለማ ላንቃሞ



ማይ ማልጌ



ምትኩ ፋኖሴ



ሶሎሞን ካምሶ



ሶሎሞን ዘገየ



ተሰማ አርጎ



መስፍን ቡጫሳ



ተስፋ ሄታሮ



ዘሪሁን ዘነበ



ሰንበቶ ማሞ

### 4.4.4. የአካል ጉዳት (ማቁሰል)

የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 16 ‹‹ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው›› ሲል ይደነግጋል፡፡ የሰዎች የአካል ደኅንነት የመጠበቅ መብት የማይደፈርና የማይገሠሥ መሆኑን የሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 14 ያረጋግጣል፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ መንግሥት ባለማስከበሩ በሲዳማ ዞን በ11/11/2011ዓ.ም ‹‹ኤጀቶ›› በተባለ ሥያሜ የተሰባሰቡ ወጣቶች የፈጸሟቸውን ብሔር ተኮር ጥቃቶች ለማስቆም ወደ ሥፍራው የተሠማራ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በወሰዱት ርምጃ ምክንያት በሚከተሉት ግለሰቦች ላይ የአካል ጉዳት ደርሷል፡፡

**ሠንጠረዥ 2 የአካል ጉዳት**

| ተ.ቁ | የቆሰለው ሰው ስም | ዕድሜ | ድርጊቱ የተፈጸመበት | የጉዳቱ ዓይነት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | ቀን | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሰሎሞን ወንደሬ | 21 | 12/11/11 | ታፋው ላይ በጥይት የተመታ | |
| 2 | አበበች ሙላቱ | 18 | 11/11/11 | ቂጡ ላይ በጥይት የተመታ | |
| 3 | ታምራት ብርሃኑ | | 11/11/11 | እግሩ ላይ በጥይት የተመታ | |
| 4 | ሹፌሪ ጫሌያምሩ | 18 | 12/11/11 | ታፋው ላይ በጥይት የተመታ | |
| 5 | ሳሙኤል ኤልያስ | 26 | 12/11/11 | ቀኝ እግሩ ላይ በጥይት የተመታ | |
| 6 | ተስፋዬ ሾክለ | 20 | 12/11/11 | ቀኝ እግሩ ላይ በጥይት የተመታ | |
| 7 | መላኩ አሰፋ | 15 | 12/11/11 | ቀኝ እግሩ ላይ በጥይት የተመታ | |
| 8 | ማሪማ ዱካ | 25 | 12/11/11 | ቀኝ ጎኑ በጥይት የተመታ | |
| 9 | በረከት ኢካሞ | 21 | | የግራ እጅ መቆረጥ | ሸበዲኖ ወረዳ ሞርቾ ነጋሽ ቀበሌ |
| 10 | አበበ ሙላቱ | 18 | | የግራ እግር ታፋ አጥንት ስብራት | ›› |
| 11 | ደቃማ ቤሞሌ | 30 | | የቀኝ እግር መቆረጥ | ›› |
| 12 | ታምራት ብርሃኑ | 20 | | ግራ ትከሻውና ቀኝ እጅ ስብራት | ›› |
| 13 | ቦሻ ቦቴ | 35 | | ትከሻው ላይ በጥይት ተመትቶ የቀኝ እጁ ሽባ ሆኗል | |
| 14 | አጋምሳ አለና | 36 | | | ›› |
| 15 | ኤዶአ ፈርሶ | 38 | | ------ | ማልጋ ወረዳ |
| 16 | ሻለቃ ተሻለ | 40 | | | ›› |
| 17 | ዶክሌ ገፎ | 39 | | | ›› |
| 18 | ሙሴ ቃሬ | 35 | | | ›› |
| 19 | ጥሩነህ ጫሪሶ | 37 | | | ›› |
| 20 | ድካሪ ሌዲሞ | 42 | | | ›› |
| 21 | ሽሎታ ሽብሩ | 40 | | | ›› |
| 22 | ላሊሞ ያዋ | 45 | | | ›› |
| 23 | ዓለሙ ጋሹራ | 35 | 12/11/2011 | በቀኝ በኩል በጀርባው ላይ በጥይት መመታት | ሀገረ ሰላም |
| 24 | መኮንን ከታ | 14 | 12/11/2011 | በቀኝ እጁ ላይ በክንዱ ላይ በጥይት መመታት | ሀገረ ሰላም |
| 25 | አጉቴ ቆጮ | 18 | 12/11/2011 | ግራ ታፋው ላይ ከበስተጓላ በጥይት | ሀገረ ሰላም |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | መመታት | |
| 26 | ተሻለ ሽዴ | 18 | 11/11/2011 | በቀኝ እግር ጉልበቱ ላይ በጥይት መመታት | ሀገረ ሰላም |
| 27 | ብፋቶ ብርሃኑ | 20 | 12/11/2011 | የግራ ኩላሊቱ በጣም በመጎዳቱ ተቆርጦ ወጥቷል፣ ጣፊያው ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበት በተደረገለት ቀድዶ ሕክምና ተርፏል፣ አንጀቱ ላይ በደረሰው ጉዳት የተጎዳው ክፍል ተቆርጦ ከወጣ በኂላ ሦስት ጊዜ ከፍተኛ የቀድዶ ሕክምና ተደርጎለታል | ሀገረ ሰላም |
| 28 | ማሪሞ ዲካ ላታሞ | --- | 12/11/11 | በትንሹ አንጀቱ ላይ ሦስት ጊዜ ቀድዶ ሕክምና ተደርጎለታል | ይርጋ ዓለም |
| 29 | ተስፋዬ ሽክሌ አርጋታ | 18 | ---- | በቀኝ እግሩ ጉልበቱ ላይ በጥይት መመታት | ሀገረ ሰላም |
| 30 | አደራ ሀመሶ | 45 | 13/11/11 | ጭንቅላቱ ላይ በጠርሙስ ተመትቶ መፈንከት | ሀገረ ሰላም |
| 31 | ከበደ ናራሞ | 30 | 13/11/11 | ጭንቅላቱ ላይ በጥይት ተመትቶ በደረሰበት ከባድ ጉዳት ምክንያት መናገርና መንቀሳቀስ ተሥኖታል | ሀገረ ሰላም |
| 32 | ተገኝ መንዱሬ | 12 | 12/11/2011 | በቀኝ እግር ታፋው ላይ በጥይት የተመታ | ሀገረ ሰላም |
| 33 | ወንዱ አሰፋ | 25 | 12/11/2011 | በቀኝ እጁ ክንዱ ላይ በጥይት ተመትቶ መቁሰል | ሀገረ ሰላም |
| 34 | ታደሰ መኑ | 24 | 12/11/11 | የቀኝ እግሩ ላይ | ሀገረ ሰላም |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | | | በጥይት የተመታ | |
| 35 | ታሰፈ ጨሮ ሀንቃ | 32 | 11/11/11 | የግራ እግሩ በጥይት የተመታ | ሀገረ ሰላም |
| 36 | ሹንዴ ኢሼ | 22 | 12/11/11 | በግራ እግሩ ታፋ ላይ በጥይት የተመታ | ሀገረ ሰላም |

***<u>ማስታወሻ፡-</u>*** *ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ የቀረበው የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ዜጎች ዝርዝር ከሁላ ሆስፒታል፣ ከይርጋ ዓለም ሆስፒታል፣ ከወረዳ ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም ከፖሊስ የተገኘ ነው፡፡*

### 4.4.5. የንብረት ውድመት

ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 17 ማንኛውም ሰው ብቻውንም ሆነ ከሌሎች ጋር በመተባበር የንብረት ባለቤት የመሆን መብት እንዳለውና ማንም ሰው በዘፈቀደ ንብረቱን እንዲያጣ እንደማይደረግ ያረጋግጣል፡፡ የኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ እንደሚከበርለት/እንደሚከበርላት ይደነግጋል፡፡ ነገር ግን በሲዳማ ዞን ‹‹ኤጀቶ›› በተባለ ሥያሜ የተሰባሰቡ ወጣቶች በ11/11/2011ዓ.ም በፈጸሟቸው ብሔር ተኮር ጥቃቶች ምክንያት የዜጎች መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድ ድርጅቶች እንዲሁም የግል ንብረቶች ወድመዋል፡፡ ጥቃቱ በተፈጸመባቸው ወረዳዎችና የከተማ መስተዳድሮች የተቋቋሙ የንብረት ገማች ኮሚቴዎች የሠሩት ግምት እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | የንብረት ውድመቱ የተፈጸመበት ሥፍራ | የውድመቱ ግምት በኢት.ብር |
|---|---|---|
| 1 | ይርጋለም ከተማ | 110,368,501 |
| 2 | አለታ ወንዶ ከተማ | 97,991,313 |
| 3 | ዳሌ ወረዳ | 10,886,611 |
| 4 | አለታ ጩኮ ከተማ | 2,337,259 |
| 5 | ማልጋ | 5,588,395 |
| 6 | ሸበዲኖ ወረዳ | 51,527,574 |
| 7 | ቦና ዙሪያ | 1,164,964 |
| 8 | አርቤጎና ወረዳ | 6,333,517 |
| 9 | ወንዶ ገነት | 268,992 |
| 10 | ሁላ | 44,640,460 |
| 11 | ጭሮኒ | 3,769,000 |
| 12 | ለኩ ከተማ | 27,006 |
| | ድምር | 334,903,592 |

### 4.4.6. በኃይማኖት ተቋማት ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች

1. ቦና ዙሪያ ወረዳ የሚገኝ በሣር ክዳን የተሠራ መስጊድ ተቃጥሏል፡፡

2. ቦና ዙሪያ ወረዳ የሚገኘው ዶያ ቅዱስ ሚካኤል ሙሉ በሙሉ ተቃጥሎ ሁለት ሚሊየን ሰባት መቶ ሺህ አራት መቶ ሰማንያ ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል፡፡

3. ሁላ ወረዳ ገተማ ቀበሌ የሚገኘው ገተማ ገብረ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ተቃጥሎ አንድ ሚሊየን ሁለት መቶ ሰባ ሦስት ሺህ አንድ መቶ ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል፣

4. ጭሮኒ ወረዳ የሚገኘው ጭሮኒ ቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ሙሉ በሙሉ ተቃጥሎ አንድ ሚሊየን ዐሥራ ሦስት ሺህ ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል፣

5. ሁላ ወረዳ ሉዳ ቀበሌ የሚገኘው ሉዳ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በደጀ ሰላሙ ላይ በተፈጸመ ቃጠሎ አራት መቶ ሰባት ሺህ አራት መቶ ሰማንያ አራት ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል፣ አራት መቶ ዐርባ ሁለት ሺህ አራት መቶ ዐሥራ ዘጠኝ ብር የሚገመት ንብረት ተዘርፏል፣

6. ሀገረ ሰላም ከተማ የሚገኘው የሀገረ ሰላም ቅድስት ኪዳነ ምሕረት ቤተክርስቲያን በተፈጸመበት ቃጠሎ አምስት ሚሊየን ሰባት መቶ ሠላሳ ሦስት ሺህ ሦስት ብር የሚገመት ንብረት ወድሟል፣ 65 ሺህ ስድስት መቶ ብር የሚገመት ንብረት ተዘርፏል፣

<u>ማጠቃለያ</u>

በዚህ ክፍል ሥር ለቀረቡ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ዋነኛው መንሥዔ የሲዳማ ሕዝብ ለዘመናት ሲያቀርብ የቆየው በክልል የመደራጀት ጥያቄ በወቅቱ ተገቢ ሕጋዊ ምላሽ አለማግኘቱ ነው፡፡ የኢሕአዴግ መንግሥት ለሕዝቡ ጥያቄ ተገቢ ሕጋዊ መልስ ከመስጠት ይልቅ በኃይል የማዳፈን አማራጭ ወስዶ ቆይቷል፡፡ ነገር ግን በ2010ዓ.ም በኢትዮጵያ ውስጥ የመጣውን የፖለቲካ ለውጥና በኢሕአዴግ አመራር ውስጥም የተከሰተውን የሥልጣን ሽግግር ተከትሎ የሕዝቡ ጥያቄ በተጠናከረ ሁኔታ መቅረብ መጀመሩ ይታወሳል፡፡ የፌዴራል መንግሥትም ከሕዝቡ ጋር በተለያዩ ጊዜያት በጉዳዩ ላይ ምክክር በማድረግ በሰላማዊ መንገድ ጥያቄው ምላሽ የሚያገኝበትን መንገድ ሲያፈላልግ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ የሕዝቡ ጥያቄ ከዞን ምክር ቤት አንሥቶ እስከ ፌዴሬሽን ም/ቤት ድረስ በተዋረድ ቀርቦ ሳለ የሲዳማ ዞን ባለሥልጣናት ‹‹ኤጀቶ›› በሚል ሥያሜ የተሰባሰቡ ወጣቶችን በማስተባበርና ድጋፍ በመስጠት በዞኑ በሚኖሩ የሌሎች ብሔሮች ተወላጆችና የመንግሥት ንብረት ላይ ጥቃት እንዲፈጸም በማድረግ በፌደራል መንግሥት ላይ ጫና ለመፍጠር ሞክረዋል፡፡ በዚሁም ምክንያት የበርካታ ዜጎች ሕይወት ጠፍቷል፣ አካል ጎድሏል፣ ንብረት ወድሟል፡፡

በደ/ብ/ብ/ሕ ክልል ውስጥ ከሚገኙ ዞኖችና ወረዳዎች መካከል ራሳቸውን ችለው በክልልና በዞን ለመደራጀት ጥያቄዎች መቅረባቸው ይታወቃል፡፡ መንግሥትም ‹‹ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን መብት አለው›› ከሚለው ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ጋር በማይጣረስና ዜጎችን ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተጋላጭ በማያደርግ መልኩ ለጉዳዩ መፍትሔ መፈለግ ይኖርበታል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በሐገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ ጊዜያት ብሔር ተኮር የሆኑ ጥቃቶችና ግጭቶች በተለያዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ሲቀሰቀሱና የበርካታ ወገኖች ሕይወት ሲጠፋ፣ አካል ሲጐድል፣ እንዲሁም ሰላማዊ ዜጐች ከመኖሪያቸው ሲፈናቀሉና ንብረት ሲወድም እንደነበር ይህም ጉዳይ በቂ ትኩረት፣ ዘለቄታዊና ሕጋዊ መፍትሄ በአስቸኳይ እንዲሰጠው በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው የተለያዩ መግለጫዎቹ ከክልል እስከ ፌደራል እርከን ለሚገኙ የመንግሥት አካላት ሲያሳውቅና ሲያሳስብ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

በሐገራችን ብሔር ተኮር ለሆኑ ጥቃቶችና ግጭቶች በቂ ትኩረት አልተሰጣቸውም። ለግጭቶቹ መነሻ የሆኑ ችግሮችን ኀብረተሰቡ በተለያዩ መንገዶች ለመንግሥት ሲያስተላልፍ ቢቆይም ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎችና ቅሬታዎች በመንግሥት በኩል በእውነተኛነት በማዳመጥ ለግጭቶቹ መቀስቀስ ምክንያት የሆኑትን መነሻ ችግሮች በማጥናት፣ ፖለቲካዊና ሕጋዊ ርምጃዎችን በመውሰድ፣ በጥቃቶቹና በግጭቶቹ ውስጥ እጃቸው ያለበት አካላትን ተጠያቂ በማድረግ፣ ዜጎችን በሐገራቸው በእኩልነትና በሰላም በፈለጉት ቦታ የፈለጉትን ሥራ ሠርተው የመኖር ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻቸው ተከብሮ እንዲኖሩ በማረጋገጥ በኩል መንግሥት ተገቢውን ጥረት እያደረገ ነው ለማለት አያስደፍርም።

በዚህ ረገድ መንግሥት ችግሮች ከመከሰታቸውና የሰው ሕይወት ጠፍቶ የአካል ጉዳትና ንብረት ውድመት ከማስከተላቸው በፊት በቂና አስተማማኝ፣ ተቋማዊና ዘላቂ የሆነ ለዜጎች ዋስትና የሚሰጥ እርምጃ መወሰድ ላይ ገና ብዙ ይቀረዋል። ችግሮቹ ከተፈጸሙም በኋላ ተጠያቂነትን የማስፈን፣ የዜጐችን የሕይወትና የአካል ደኅንነት የመጠበቅ፣ ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ ኑሮን የመመሥረት ሕገ መንግሥታዊ መብት በማረጋገጥ ረገድ በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ድክመት ይታያል።

በአገራችን በተለያዩ አከባቢዎች ዜጎች በብሔር ማንነታቸው ብቻ ጥቃቶች እየተፈጸመባቸው የብዙ ወገኖች ሕይወት አልፏል፣ የአካል ጉዳት ደርሷል፣ ሚሊዮኖች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፣ በርካታ ንብረት ወድሟል። ማንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በፈለገበት የሐገሪቱ ክፍል ተዘዋውሮ ኑሮውን የመመሥረት እና ሠርቶ የመኖር ሕገ-መንግሥታዊ መብት አለው። ከዚህ በተቃራኒ በማን አለብኝነት የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች በተደራጁና በታጠቁ ኃይሎች እየተጣሰ ቢገኝም መንግሥት እነዚህን ሰብዓዊ ጥሰቶች ማስቆምና የዜጎችን ሰላምና ደኅንነት ከማስጠበቅ ይልቅ ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ ምላሽ ለመስጠት በመሞከር ላይ ያተኮረ ይመስላል። ብሔር ተኮር ጥቃቶችና ግጭቶች ላይ እጃቸውን ያስገቡና ዋና ተዋናዮች በሙሉ ተይዘው ለሕግ ባለመቅረባቸውና ተመጣጣኝ የሆነ አስተማሪና ሕጋዊ እርምጃ መንግሥት ባለመውሰዱ ነገሩ ከቀን ወደ ቀን እየሰፋ ሄዶ በአሁኑ ወቅት በሐገራችን ሰላምና መረጋጋት ላይ ከፍተኛ ሥጋት እየፈጠረ ይገኛል።

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በሕዝብ የሚነሡ የተለያዩ ጥያቄዎች በተለይም የሕግ የበላይነት የማረጋገጥ ጥያቄዎች፣ የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎች፣ የሰብዓዊ መብቶችንና የተለያዩ ጥያቄዎችን በወቅቱ በዴሞክራሲያዊና በሕጋዊ መንገድ ከሕዝብ ጋር በመነጋገር ዘለቄታዊ መፍትሔ መንግሥት መፈለግ ይኖርበታል።

የተለያየ ሥያሜ በመያዝ በብሔር ማንነት ዙሪያ የተሰባሰቡ የወጣቶች ቡድኖች በንጹሐን ዜጎች ላይ እየፈጸሙት ያሉት ግድያና መጠነ ሰፊ ጥፋት በሚመለከታቸው የክልል እና የፌዴራል መንግሥት አካላት አስቸኳይ ትኩረትና ሕጋዊ መፍትሄ እንዲሰጠው ኢሰመጉ በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው የተለያዩ መግለጫዎቹ ሲያሳስብ መቆየቱ ይታወቃል።

እነዚህ መደበኛ ያልሆኑ የወጣቶች አደረጃጀቶች ለዜጎች ሕይወት መጥፋት፣ አካል ጉዳት፣ ለከፍተኛ የንብረት መውደም ብሎም ለሐገሪቱ አለመረጋጋት ምክንያት ሆነዋል። የሚመለከታቸው የክልልም ሆነ የፌዴራል የመንግሥት ተቋማት ለዚህ ከባድ ችግር በቂ ትኩረት ሰጥተው ሕጋዊና አስተማማኝ ርምጃ በመውሰድ የዜጎችን በሰላም የመኖር፣ ወጥቶ የመግባትና ንብረት የማፍራት መብቶቻቸው ላይ ለተጋረጠው ከፍተኛ አደጋ መፍትሄ ሊሰጡ እንደሚገባ ኢሰመጉ ያምናል።

## 4.5. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን ለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ ውስጥ መኖሪያ ቤታቸው የፈረሰባቸው ዜጎች ጉዳይ

ከአዲስ አበባ ሰሜን ምስራቅ በ21 ኪ.ሜ እርቃ የምትገኘው ለገጣፎ-ለገዳዲ ከተማ በሰሜንና በምስራቅ የበረህ ወረዳ በምዕራብ አዲስ አበባ ከተማ የሚያዋስኗት ናት፡፡ ከተማዋም 2431 ሄክታር የመሬት ስፋት ያላትና ሁለት ቀበሌዎችን የያዘች ናት፡፡ በ1998 ዓ.ም አካባቢ 18,177 የህዝብ ብዛት የነበራት የለገ-ጣፎ ለገዳዲ ከተማ ነዋሪዎች በብዛት በከተማዋ በሚገኙ የተለያዩ ፋብሪካዎች ውስጥ ተቀጥረው በሚያገኙት ገቢ የሚተዳደሩ ሲሆኑ፣ የተወሰኑት በተለያየ የንግድ ስራ፣ ጥቂቶቹ ደግሞ በከተማዋ ዙሪያ በግብርና ስራ ተሰማርተው ኑሮአቸውን ይመራሉ፡፡

ከዚህ ቀደም፣ በተደጋጋሚ በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ‹‹ሕገ-ወጦች ናቸሁ›› በማለት ዜጎች ጥሪታቸውን ቋጥረው የገነቡዋቸውን መኖሪያ ቤቶች ማፍረስ የዜጎችን ችግር እንዲባባስ እንደሚያደርገው እንዲሁም እነዚህ ዜጎች ቤት ሰርተው፣ የውሀና የመብራት መሥመሮች በማስገባት፣ በአካባቢው የተለያዩ የአስተዳደርና የልማት እንቅስቃሴ ሲሳተፉ ቆይተው ተስፋም አድርገው የዕለት ተዕለት ሕይወታቸውን ተረጋግተው መኖር ሲጀምሩ በላያቸው ላይ ቤታቸውን ማፍረስ አስቀድሞ የመከላከያ እርምጃዎችን መውሰድ እየተቻለ ከሰብዓዊነት አንጻር ተገቢ እንዳልሆነ ኢሰመጉ በተለያዩ ጊዜያት ሲገልፅ ቆይቷል፡፡

ከመንግስት አካ ያ ለመገናኛ ብዙሃን በተሰጠው መልስ መሰረት መኖሪያ ቤቶቹ የፈረሱት አካባቢው ለአረንጓዴ ተክሎች ልማት ስለሚፈለግ በሚል ምክንያት እንደሆነ ኢሰመጉ ለመገንዘብ ችሏል፡፡ ሆኖም ግን ኢሰመጉ የቀረበለትን አቤቱታ ለማረጋገጥ ለከተማው ከንቲባ አስተዳደር ደብዳቤ በቁጥር ER3/M4/02/19 14/06/2011 በተፃፈ ደብዳቤ ጠይቋል፡፡ እንዲሁም በተደጋጋሚ በአካል በመሄድ ጭምር ጥረት ቢያደርግም ይህ ሪፖርት እስከሚጠናቀርበት ጊዜ ድረስ ምላሽ ማግኘት አልቻለም፡፡

ኢሰመጉ መኖሪያ ቤታቸው ከፈረሰባቸው ሰዎች መካከል ከቀረበለት ማመልከቻ በመነሳት ባከናወነው ምርመራ ለማረጋገጥ እንደቻለው ለገዳዲ ለገጣፎ ቀበሌ 01 እና 02፣ በሚገኙ የተለያዩ መንደሮች ማለትም ገዋሳ መንደር፣ ቀበሌ ጃል ዋሻ፣ ጭለሎ መንደር (ጉራጌ ሰፈር)፣ ደምበል 140፣ ቡርቃ መንደር፣ ከረሜላ ፋብሪካ መንደር፣ ደምበል ሚሽን ዞን፣ ሞሱማ ጉዲና፣ ገዋሳ ጃል ዋሻ ነዋሪ የነበሩ እና ቁጥራቸው ከ419 በላይ የሆኑ አባወራዎች በከተማው አስተዳደር ቤት አፍራሽ ግብረ ኃይል የካቲት 12 ቀን 2011 ዓ.ም እንደ ፈረሰባቸው ኢሰመጉ አረጋግጧል፡፡

ቤታቸው ከፈረሰባቸው ሰዎች መካከል በርካታዎቹ የነዋሪነት መታወቂያ ያላቸው፣ በተለያዩ ሀገራዊና አካባቢያዊ ምርጫዎች የተሳተፉ፣ የመብራትና ውኃ መሥመር የተዘረጋላቸው፣ በተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ሲሳተፉ የቆዩና የተለያዩ ቋሚ ንብረት አፍርተው ሰላማዊ ኑሯቸውን እየመሩ ባለበት ወቅት ቤታቸው እንዲፈርስና ሰላማዊ ኑሯቸው እንዲናጋ መደረጉ አግባብ እንዳልሆነ ኢሰመጉ ያምናል፡፡

መንግስት በየጊዜው እየጨመረ የመጣውን የዜጎችን የመጠለያ ችግር በትኩረት በቂ በሆነ አሰራር ከመፍታት ይልቅ ጥሪታቸውን ሰብስበው የሰሩትን ቤት ማፍረሱ ተገቢ ካለመሆኑ በላይ የዜጎችን መጠለያ የማግኘት መብትንም የሚፃረር ነው፡፡ ስለሆነም፣ ለዚህ አንገብጋቢና ጊዜ የማይሰጥ ችግር ከህዝብ ጋር በመወያየት በዘላቂ ሁኔታ መፍታት እንዳለበት ኢሰመጉ ያሳስባል፡፡

## 4.6. በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ሐረር ከተማ ጥር 10 እና 11 ቀን 2012 ዓ.ም የደረሱ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች

በሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ሐረር ከተማ ከጥር 10 - 12 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ባሉት ተከታታይ ቀናት የጥምቀት ዋዜማ (ከተራ) እና የጥምቀት ክብረ-በዓላትን አስታኮ በተፈጠረ ኹከትና ብጥብጥ የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች በወሰዱት የኃይል እርምጃ እና መደበኛ ባልሆኑ የወጣቶች ስብስብ በንጹኃን ሰዎች ላይ በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ተፈጽመዋል። ጥር 10 ቀን 2012 ዓ.ም ሐረር ከተማ፣ ሀኪም ወረዳ ልዩ ስሙ አራተኛ በሚባል አካባቢ ወጣቶች ለጥምቀት በዓል ዝግጅት በማድረግ ላይ እያሉ፤ ከረፋዱ 4፡00 አካባቢ ጀምሮ በቡድን የተደራጁ ሌሎች ወጣቶች አውራ መንገዶችን በድንጋይ እና በጎማ በመዝጋት፣ ለበዓሉ ታስበው የተሰቀሉ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን መለያ አርማ ያለባቸውን ባንዲራዎችና የተለያዩ ዓይነት ሪቫኖች ከተሰቀሉበት በማውረድ የበዓሉን አከባበር ለማወክ ሙከራ አድረገው ነበር።

በእለቱ ከቀኑ 8፡30 ጀምሮ በርካታ ቁጥር ያለው ምዕመን ታቦታቱን በዓሉ ወደሚከበርበት ቦታ አጅቦ ለመውሰድ ጉዞ የጀመረ ቢሆንም፤ በተለይም የቅዱስ ገብርኤልና የቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦታት የሚሄዱበት መንገድ በተደራጁ ወጣቶች በድንጋይና በጎማ እንዲዘጋ ተደርጓል። በወቅቱ ተከስቶ በነበረው ግርግር ምክንያት ሁኔታውን ለማረጋጋት በሚል ከፖሊስ በተተኮሱ ጥይቶችና የአስለቃሽ ጭስ ጥይቶች ምክንያት ከስምንት ያላነሱ ንጹኃን ሰዎች ላይ የአካል ጉዳት የደረሰ መሆኑን፣ በሚሊዮን የሚገመት የግለሰቦች የንግድና መኖሪያ ቤቶች እና ንብረቶች መውደሙን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስትያን የምስራቅ ሐረርጌ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት በደብዳቤ ቁጥር 2/752/1705/2012 በቀን 6/12/12 ለኢሰመጉ በተጻፈ ደብዳቤ አሳውቋል።

ይህ ድርጊት ሲፈጠር በቦታው የነበረው የክልሉ የፀጥታ ኃይል አጥፊዎችን መከላከል እና ሕገ-ወጥ የሆኑ ድርጊቶችን ማስቆም ሲገባው፤ የአስለቃሽ ጭስ ጥይቶችን ወደ ሕዝብ በመተኮስ ነገሮች እንዲባባሱና ጉዳት እንዲደርስ ማድረጉን ኢሰመጉ በወቅቱ በስፍራው ከነበሩ የዓይን እማኞችን ቃል ለመረዳት ችሏል።

በማግስቱ ጥር 11 ቀን 2012 ዓ.ም ደግሞ ከበዓሉ ስነ-ስርዓት መጠናቀቅ በኋላ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ ታቦታቱን በማጀብ ወደየመጡበት አብያተ-ክርስቲያናት በመሸኘት ላይ እያለ፤ በድጋሚ የቅዱስ ገብርኤልና ቅዱስ ጊዮርጊስ ታቦታት የሚያልፉበት በልዩ ስሙ አራተኛ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ያለ አውራ መንገድ በድንጋይና በጎማ በመዘጋቱ ምክንያት ግርግር ተፈጥሯል። በዚህም ችግሩን ለመቆጣጠር በሚል ፖሊስ በተኮሰው አስለቃሽ ጭስ ጥይት ምክንያት በንጹኃን ሰዎች ላይ የሕይወት መጥፋት እና የአካል መጉደል ጉዳቶች ደርሰዋል። ኢሰመጉ፤ ድርጊቱ በተፈጸመባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት ባደረጋቸው የምርመራ ሥራዎች በእለቱ የሚከተሉት ዋና ዋና የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ተፈጽምዋል።

**ሕገ-ወጥ ግድያ፡** ሰብሀዲን ተማም በሐረር ከተማ ቀበሌ 13 ነዋሪ የሆነ የ15 ዓመት ህጻን ሲሆን፤ ጥር 11 ቀን 2012 ዓ.ም ሐረር ከተማ፣ ሀኪም ወረዳ፣ ልዩ ስሙ አራተኛ ፈዲስ መንገድ እየተባለ በሚጠራ አካባቢ፣ ስማርት ህንጻ ውስጥ እያለ በአካባቢው የተነሳ ረብሻን ተከትሎ ከፖሊስ በተተኮሰ የአስለቃሽ ጭስ ጥይት ጭንቅላቱን መመታቱን በቦታው የነበሩ የዓይን እማኞች ለኢሰመጉ

አረጋግጠዋል። ህጻን ሰብሀዲን በደረሰበት ጉዳት ለአንድ ሳምንት ያህል ሕክምና ሲደረግት ቢቆይም ሕይወቱ ሊተርፍ አልቻለም። ኢሰመጉ ባደረገው ማጣራት ለህጻን ሰብሀዲን ሞት ተጠያቂ እንዲሆን የተደረገ አንድም አካል የለም።



**ህጻን ሰብሃዲን ተማም**

**አካል ጉዳት፡** ፍጹም ለገሰ በሐረር ከተማ ቀበሌ 18 ነዋሪ የሆነ የ25 ዓመት ወጣት ነው። ወጣት ፍጹም ጥር 11 ቀን 2012 ዓ.ም ከእለቱ 6፡00 አካባቢ በቤተ-ክርስቲያን የመንፈሳዊ ዝማሬ አገልግሎት ላይ ነበር። በእለቱ የተነሳውን ረብሻ ተከትሎ ሐረር ከተማ፣ ሀኪም ወረዳ፣ ልዩ ስሙ አራተኛ ቶታል ፊት ለፊት ከፖሊስ በተተኮሰ የአስለቃሽ ጭስ ጥይት ዓይኑን በመመታቱ ምክንያት የግራ ዓይኑ ሙሉ በሙሉ የመፍሰስ ጉዳት ደርሶበታል። ወጣት ፍጹም ለደረሰበት አካላዊ ጉዳት ምንም ዓይነት ካሳም ሆነ የሕክምና ወጪ ድጋፍ ያልተደረገለት ከመሆኑም በላይ፤ ድርጊቱን የፈጸመው ሰው ላይ የተወሰደ እርምጃ የለም።

ወጣት ተመስገን ይሁኔ ደግሞ በሐረር ከተማ ቀበሌ 18 ነዋሪ የ32 ዓመት ወጣት ነው። ወጣት ተመስገን ጥር 12 ቀን 2012 ዓ.ም በንግድ መደብሩ ውስጥ እያለ ብዛት ያላቸው ወጣቶች መጥተው ከሱቁ ሳይወጣ መላው ሰውነቱ በእሳት እንዲቃጠል በመደረጉ፤ በእጆቹ፣ በእግሮቹ፣ በፊቱ እና በሰውነቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ የመቃጠል ጉዳት ደርሶበታል። ይህ መግለጫ በሚዘጋጅበት ወቅት ወጣት ተመስገን ላይ ጉዳት ያደረሱ ሰዎች ለሕግ ያልቀረቡ መሆናቸውን ኢሰመጉ ለማረጋገጥ ችሏል።

<u>**የተጎጂዎችን አካል ጉዳት የሚያሳዩ የፎቶ ማስረጃዎች በከፊል**</u>

 

ከዚህም በተጨማሪ ከጥቅምት 10 — 12 ቀን 2012 ዓ.ም ድረስ ተፈጥሮ በነበረው ረብሻ ምክንያት ሐረር አራተኛ ልዩ ስሙ መጠለያ በሚባው አካባቢ የሚገኙ ከ240 በላይ ነዋሪዎች መደበኛ ባልሆነ መንገድ የተደራጁ ወጣቶች በሚያደርሱባቸው ዛቻና ማስፈራሪያ፣ ብሎም በቤት ንብረታቸው ላይ በደረሰ ዝርፊያ የተነሳ ከመኖሪያ ቤታቸው ተፈናቅለው በቅዱስ ገብርኤል ቤተ-ክስቲያን ተጠልለው የነበሩ መሆኑን ሀገረ ስብከቱ ከላይ በገለጽነው ደብዳቤ አሰውቋል፡፡ በቤት ንብረታቻው ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦችና ተቋማት ከክልሉ መንግሥት ምንም ዓይነት ድጋፍ ያልተደረገ መሆኑን ኢሰመጉ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡ በወቅቱ ተፈጥሮ በነበረው ረብሻ ምክንያት በቤት ንብረታቸው ላይ ጉዳት በርካታ ሰዎች መካከል፤ የጥቂት ሰዎች ዝርዝር የሚከተለውን ይመስላል፡፡

| ተ.ቁ | ሙሉ ሥም | ጾታ | እድሜ | ከተማ | ቀበሌ | ሥራ | የደረሰው ጥፋት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ሲሳይ ገ/ኪዳን | ወ | 43 | ሐረር | 17 | የፋብሪካ ሠራተኛ | ዝርፊያ እና ውድመት |
| 2 | አቶ ሲሳይ ዋጂ | ወ | 60 | ሐረር | 17 | ነጋዴ | ዝርፊያ እና ውድመት |
| 3 | አቶ ዘመነ ተሰፋ | ወ | 41 | ሐረር | 17 | የግል | መኖሪያ ቤትና ንብረት ቃጠሎ |
| 4 | አቶ መለስ ክፍሌ | ወ | 34 | ሐረር | 17 | ነጋዴ | ዝርፊያ እና ንብረት ውድመት |
| 5 | አቶ ታጁዲን መሀመድ | ወ | 45 | ሐረር | 17 | ነጋዴ | ንበረት ውድመት |
| 6 | ወ/ሮ ሒንዲያ ኢድሪስ | ሴ | 37 | ሐረር | 13 | ነጋዴ | ንብረት ውድመት |
| 7 | አቶ ሰለሞን አለማየሁ | ወ | 34 | ሐረር | 17 | ነጋዴ | ንብረት ውድመት |

## 4.7. ልዩ ልዩ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች

- **ሕገ-ወጥ እስር እና ድብደባ**

አቶ ተፈራ አለሙ በጎሰው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ ደቡብ ወሎ ዞን፣ ደሴ ከተማ አገር ግዛት ክ/ከ፣ ቀበሌ 08፣ በቤት ቁጥር 458 ነዋሪ ሲሆኑ፤ በመንግስት የሥራ ኃላፊነት ላይ የሚገኝ ግለሰብ ነበር። ግለሰቡ ኃላፊነቱን ተጠቅሞ ሕዝብ የማረጋጋት ሥራ እንዲሰራለት በወቅቱ የነበረው የኢህአዴግ ስርዓት ቢጠይቀውም፤ መግባባት ባለመቻላቸው ከደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን አስ/ጽ/ቤት በቀን 16/1/87 በተጻፈ ደብዳቤ ከሥራ ኃላፊነቱ እንዲታገድ ተደርጓል። ከዚህም አልፎ በወቅቱ በነበረው ፖለቲካዊ አለመረጋጋት ሳቢያ ወደ አምባሳል ወረዳ ውጫሌ ከተማ ሄደው ለመኖር ተገድደዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ህዳር 22 ቀን 1989 ዓ.ም በወቅቱ የሕዝብ ደህንነት ተጠሪ በነበረው አቶ የሱፍ፣ በወረዳው የደህንነት ኃላፊ (ስሙ ለጊዜው አልታወቀም) እና የወረዳው ምክትል አስተዳዳሪ የነበረው አቶ አበበ ከምሽቱ 3፡00 ሰዓት አካባቢ በአቶ ተፈራ አለሙ መኖሪያ ግቢ በመግባት፤ በጥፊ በመምታት እና ወደ ኋላ በማሰር ወደ ደሴ ከተማ ደህንነት ቢሮ እንደወሰዱት፣ በዛም *‹‹በህቡዕ ከተደራጁ ሰዎች ጋር ያለህ ግንኙነት ምንድን ነው?››* እያሉ በመጠይቅ እስከ ለሊቱ 8 ሰዓት ድረስ ልብሱን በማስወለቅ ብረት ላይ ዘቅዝቀው አስረው አቆይተውታል።

ከዚህም ባለፈ ለሰብዓዊ ክብር ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ መጸዳጃ ቤት ውስጥ ጥለውት የነበረ ሲሆን ለመውጣት በሚሞክርበት ጊዜ በሽጉጥ ሰደፍ ተመትቶ የጎን አጥንቱ ተዛብቷል። በዚህም ሳያበቃ *‹‹የመአህድ ኃላፊ ሆኜ ለህዝቡ በመስራቴ ይቅርታ ይደረግልኝ››* ብለህ እመን በሚል ለቀናት የማያቋርጥ ድብደባ ደርሶበታል። ድብደባው ባደረሰበት ድካም የደብዳቤውን ምንነት በማይለይበት ስቃይ ውስጥ ሆኖ የፈረመ በመሆኑ ከቀናት በኋላ በከባድ ማስጠንቀቂያና ትዕዛዝ ቤቱ ውሰደው ጥለውታል። በመቀጠልም ወደ ሥራው እንደሚመለስ እና አባላቶችን ሰብስቦ ጥናት መስጠት እንዲጀምር ትዕዛዝ ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም፤ አካባቢውን ለቆ ወደ አዲስ አበባ ሸሽቷል።

ከላይ የሰፈረው ግፍ ከሀገሪቱ ሕግጋት፣ ከሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች እና ከሰብዓዊ ርህራሄዎች ፍጹም ያፈነገጠ እና በማንኛውም የሰው ልጅ ላይ ሊፈጸም የማይገባው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ነው። ማንኛውም ሰው በፖለቲካ፣ በኃይማኖት፣ እንዲሁም በሀሳብ የፈለገውን መርጦ የመከተል መብት ያለው መሆኑን፣ በሕግ የዳኝነት ስልጣን በተሰጠው አካል ትዕዛዝ መሰረት ካልሆነ በቀር የአካል ነጻነቱን የማያጣ መሆኑ፣ እና በጥፋት ተጠርጥሮ ቢያዝም እንኳን ሰብዓዊ ክብር በተሞላው አያያዝና እንክብካቤ የመያዝ መብት የተሰጠው መሆኑን በተለያዩ ሕግጋት ተደንግጎ የሚገኝ ነው።[2] ከዚህ አንጻር በዚህ ግለሰብ ላይ የደረሰውን ኢ-ሰብዓዊ አያያዝ የሚመለከተው አካል አጣርቶ ፍትሕ እንዲሰጠው ኢሰመጉ ይጠይቃል።

- **ፍትህ ማጣት**

አመልካች አቶ ሙሉ በቀለ በፊንፊኔ ዙሪያ አቃቂ ወረዳ ገላን አራብሳ ገበሬ ማኅበር ከአባታቸው በወረሱት መሬት እና የእህታቸውን የእርሻ መሬት በስጦታ ተቀብለው ከ 1983 ዓ.ም ጀምሮ ከገበሬ ማኅበር የይዞታ ማረጋገጫ ተሰጥቷቸው ከቤተሰባቸው ጋር ሲኖሩ የነበረ ሲሆን፤ ነገር ግን የእህታቸው ልጅ ወ/ሮ መድኃኒት ታደሰ ‹‹ቦታው የእናቴ ቦታ ነውና መውረስ ያለብኝ እኔ ነኝ›› ሲሉ ለአቃቂ ወረዳ ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀርባሉ።

---

[2] የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 27, 16, 17, 18፣ የሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት አንቀጽ 7, 9 ፣ ሁሉ-አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 3, 9, 5

የወረዳው ፍ/ቤት፤ ጉዳዩን ተመልክቶ ቦታው የአቶ ሙሉ በቀለ መሆኑን የሚገልጽ ውሳኔ ሰጠ። ከዚህ በኋላ፤ ከሳሽ ወ/ሮ መድኃኒት ጉዳዩን በይግባኝ ወደ ኦሮሚያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰዱት ሲሆን፤ ፍ/ቤቱም የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻር ቦታው የይግባኝ ባይ መሆኑን ገልጾ፤ በቦታው ላይ ያለው ባህር ዛፍ ግን የመልስ ሰጪ የሚል ውሳኔ ሰጥቷል። በመቀጠለም መልስ ሰጪ የነበሩት አቶ ሙሉ ጉዳዩን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አሉ።

ጠቅላይ ፍ/ቤት የታችኛው ፍ/ቤት ውሳኔ ስህተት የለበትም በማለት ያለ በቂ ትንተኔ እና ተጠሪንም ጠርቶ ሳያከራክር የስር ፍ/ቤት ውሳኔን አጸና። አቶ ሙሉ ጉዳዩን ይዘው ወደ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ቢሆንም፤ ችሎቱ የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም ብሎ ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል።

ከዚህ በማስከትል ጉዳዩ ያመራው ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢሆንም፤ ውሳኔው ግን ተመሳሳይ ነበር። በመጨረሻም፤ የፌደሬሽን ም/ቤት የሕገ-መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በጉዳዩ ላይ የሕገ-መንግሥት ትርጉም እንዲሰጥበት የቀረበ ቢሆንም፤ አጣሪ ጉባዔው ጉዳዩ ሕገ-መንግሥታዊ ትርጉም አያሻውም የሚል ውሳኔ ሰጥቶበታል። ከዚህ በኋላ፤ በድጋሚ አመልካች አቶ ሙሉ በቀለ ለፌደሬሽን ም/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ፤ አመልካቹ በግል ይዞታቸው ላይ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ መሰረት የፍርድ ባለመብቶች ፍርዱን በሚያስፈጽሙበት ወቅት በይዞታቸው ላይ የሚገኝ ቤታቸው ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ በከፊል ፈርሶ፣ ንብረታቸውም ያለአግባብ ተወስዶ በሕገ-መንግስቱ የተረጋገጠላቸውን ንብረት የማፍራት መብታቸውን ያጡ መሆኑን በግልፅ ጠይቀዋል። ነገር ግን፤ ም/ቤቱ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም ሲል ውሳኔ ሰጥቶበታል።

ኢሰመጉ የዚህን ጉዳይ የፍ/ቤት ሒደት ለመከታተል ባደረገው ጥረት ጉዳዩ ከስር ሲጀመር የውርስ ጉዳይ ሆኖ የጀመረ ቢሆንም፤ ኋላ ላይ ግን ጭብጡን ቀይሮ አቶ ሙሉ እየተከራከሩበት ካለው የግል ይዞታቸው ውጪ ሌላ ንብረት ለመውረስ የጠየቁ አድርጎ በመረዳት፤ በፍርድ አፈጻጸም ወቅት የግል ይዞታቸውን ጭምር ተነጥቀው፣ ንብረቶቻቸውም ወድመው ግለሰቡ ለሰብዓዊ ችግር ተዳርገዋል።

ኢሰመጉ የአቶ ሙሉ በቀለን ጉዳይ በሚመለከት ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ለመመርመር ባደረገው ጥረት፤ በግል ይዞታቸው ላይ የሰሩት ባለ አራት ክፍል መኖሪያ ቤት ጣራው፣ በር እና መስኮቶቹ የፈረሱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ችሏል። በመሆኑም፤ የሚመለከተው የፍትሕ አካል የእኒህን ግለሰብ ፍትሕ ማጣት አጣርቶ ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያደርግ ኢሰመጉ ይጠይቃል።

- **ፍትሕ ማጣት**

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት፣ ምዕራብ ጎጃም ዞን፣ በጃቢ ጠህናን ወረዳ በእርግብ ቀበሮ ሜዳ ቀበሌ የሚኖሩ 457 አባወራዎች ‹‹ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ የይዞታ መሬታችንን ከሕግ አግባብ ውጪ በሆነ መንገድ ተነጥቀን በኢንቨስትመንት ሥም ለባለሃብት ተሰጥቶብናል፣ በይዞታችን ላይ የነበረን ቤትና ንብረት እንዲወድም ብሎም ንበረታችንን ትተን እንድንወጣ ድብደባና ማዋከብ ተፈጽሞብናል። በወቅቱ ችግራችንን እንዲፈቱልን ከወረዳ ጀመሮ እስከ ፌደራል መንግሥት ድረስ ያሉ አካላት ጋር ያመለከትን ቢሆንም፤ ምንም መፍትሔ አላገኘንም።›› ሲሉ ሚያዚያ 10 ቀን 2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አቤቱታቸውን ለኢሰመጉ አመልክተዋል።

አቤቱታውን ለማጣራት የኢሰመጉ ባለሙያ በቦታው ድረስ በመሄድ መረጃዎችን ለማጣረት የሞከረ ሲሆን፤ በዚህም መሠረት ገበሬዎቹ ከ1989 ዓ.ም በፊት የያዙትና በኋላም የመሬት ሽግሽግ ሲደረግ ‹‹የያዛችሁትን ይዛችሁ ትቀጥላላችሁ›› ተብለው ይዞታው እንደጸናላቸው፣ በ1990 ዓ.ም ደግሞ የመሬት ግብር እንዲገብሩ የተደረገ መሆኑን፣ በ1991 ዓ.ም ግን ይዞታው አቶ አድማሱ አበበ እና አቶ አበባው ቦጋለ ለተባሉ ባለሃብቶች በኢንቨስትመንት መሰጠቱንና ለገበሬዎቹ ካሳ ወይም ምትክ ቦታ እንዳልተሰጣቸው ኢሰመጉ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡

ዜጎች በሕገ-መንግሥቱ በግልጽ እውቅና የተሰጠው ንብረት የማፍራት መብታቸው የተጠበቀ ሆኖ ሳለ፤ አግባብ ባለው ሕግ ከይዞታ መሬታቸው ሲነሱ ደግሞ ተገቢው ካሳ ሊከፈላቸውና ምትክ ቦታ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ ነገር ግን፤ እነዚህ ገበሬዎች እስካሁን ድረስ ምትክ ቦታም ሆነ ሰካሳ ያልተሰጣቸው እና በከፍተኛ ችግር ውስጥ ያሉ በመሆኑ፤ የሚመለከተው የመንግሥት አካል ተገቢውን ድግፍና ካሳ እንዲያደርግላቸው ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

- **በኃይማኖት ተቋማት ላይ የደረሰ ጥቃት**

መግለጫው በዳሰሳቸው ጊዜያት በሐገራችን በተለያዩ አካባቢዎች የኃይማኖት ተቋማት እና የእምነት ተከታዮቻቸው ላይ ጉዳት እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡ ከእነዚህም መካከል ሀምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም በሁላ ወረዳ ዶያ ሚካኤል፣ ጭሮኒ አማኑኤል፣ ገታማ ገብረ ክርስቶስ፣ ሊዳ ገብርኤል፣ ሥላሴ ሀገረ ሰላም፣ ኪዳነ ምህረት ሀገረ ሰላም፣ ቀጨኔ ልደታ ቤተ-ክርስቲያን ቃጠሎና ዘረፋ ተፈጽሞባቸዋል፡፡ ጳጉሜ 3 ቀን 2011 ዓ.ም ደግሞ በኦሮሚያ ክልል፣ ምስራቅ ሐረርጌ ዞን፣ የመድሐኒዓለም እና የማርያም ቤተ-ክርስቲያኖች ተቃጥለዋል፡፡ የካቲት 2 ቀን 2011 ዓ.ም በደቡብ ክልል፣ አላባ ዞን ለኩ ሕይወት ብርሀን የፕሮስቴታንት እምነት ተከታዮች ቤተ-ክርስቲያን ተቃጥሏል፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት እስቴ ወረዳ መካነ-እየሱስ ከተማ የሚገኝ መስጊድ ተቃጥሏል፡፡ በሌላ በኩል፤ ታህሳስ 10 ቀን 2012 ዓ.ም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሞጣ ከተማ ውስጥ የሚገኘው ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ከቀኑ 11:30 መቃጠል መጀመሩንና የአካባቢው ነዋሪ ህዝብ ተረባርቦ እሳቱን አጥፈቶታል፡፡ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን አውድ በሚባል ቦታ የተቃጠለ መሆኑን ቤተ-ክርስቲያች በሙሉ እየተቃጠሉ ነው ተብሎ የሐሰት ወሬ ተሰራጭቷል፡፡

ከዚህ በኋላ ምሽቱን ሦስት መስጊዶች ተቃጥለዋል፣ ንብረትነታቸው የእስልምና እምነት ተካታዮች የሆኑ 70 ያህል የንግድ ሱቆች ተቃጥለዋል፣ ዝርፊያም ተፈጽሞባቸዋል፡፡ በእለቱ ንብረትነታቸው የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑ 40 ያህል የንግድ ሱቆችም ቃጠሎና የንብረት ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ ችግሩን ለመፍታት ከክልሉ ፖሊስ ኮሚሽን፣ ከክልሉ ፍትሕ ቢሮ፣ ከዞንና ከወረዳ ፍትሕ መምሪያዎች የምርመራ ቡድን ተቋቁሞ ምርመራው በገለልተኝነት እየተጣራ መሆኑን በየምስራቅ ጎጃም ዞን የሞጣ ከተማ አስተዳደር ፖሊስ ጽ/ቤት በቁጥር 1056/25-25 በ07/05/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ገልፆልናል፡፡

የሞጣ ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት በከተማችን በ10/04/2012 ዓ.ም በተፈጠረው ችግር ሐብትና ንብረታቸው የተቃጠለባቸው /የተዘረፉ/ ግለሰቦችን በመለየት የወደመባቸውን ሀብት መጠንና ዓይነት ኮሚቴ በማቋቋም፡-

- ሙሉ በሙሉ የወደመ የነገድ ድርጅት 50 ሲሆን፤ 37 የሙስሊም፣ 13 የክርስቲያን

- በከፊል የወደመ 23 ሲሆን፤ 12 የሙስሊም፣ 11 የክርስቲያን
- አነስተኛ ጉዳት የደረሰበት 20 ሲሆን፤ 11 የሙስሊም፣ 9 የክርስቲያን መሆኑን፤
- የተቃጠለ 19 ሲሆን 10 የሙስሊም፣ 9 የክርስቲያን መሆናቸውን በአጠቃላይ 112 የንግድ ድርጅቶች ጉዳት ጉዳት የደረሰባው ሲሆን፤ 70 የሙስሊም 42 የክርስቲያን መሆናቸውንና መኖሪያ ቤቶችንና የእምነት ተቋማት እንዲሁም 2 ህንጻዎች በባለሙያ የሚጠኑ መሆናቸውን የሞጣ ከተማ ከንቲባ ጽ/ቤት በቁጥር ሞ/ከ/አስ/1016/መ-3 በ23/04/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ገልጸልናል፡፡

በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት የአማራ ክልል እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት በበኩሉ፤

- 4 መስጅድ መቃጠላቸውን፤
- ንብረትነታቸው የእስልምና እምነት ተካታዮች የሆኑ 145 መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድ ድርጅቶች እና ተሽከርካሪዎች፣ ንብረትነታቸው የክርስትና እምነት ተከታዮች የሆኑ 12 ቤቶች ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡
- በአጠቃላይ በሞጣ ከተማ በ163 መኖሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ላይ የደረሰው ጉዳት ግምቱ ከ 353,979,637 ብር በላይ የሚገመት መሆኑን በቁጥር 786/14/12 በ04/06/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በኢትዮጵያ እስ/ጉ/ም/ቤት የአማራ ክልል እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ም/ቤት ገልጸልናል፡፡

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት በሞጣ ከተማ ሙስሊም ማኅበረሰብ ላይ የተፈጸመውን ጥቃት አጣሪ ልዑካን በቦታው ድረስ በመላክ ያቀረበው ሪፖርት የወደሙ ንብረቶች ግምት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| ተ.ቁ | የንብረቶች ዝርዝር | ብዛት | ግምት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | መስጂድ | 4 | 66,453,235.00 | |
| 2. | ንግድ ተቋማት | 102 | 172,918,077.00 | ንብረትነታቸው የእስልምና እምነት ተካታይ የሆኑ ሰዎች |
| 3. | መኖሪያ ቤቶች | 21 | 8,341,280.00 | ›› |
| 4. | በአክሲዮን የተገነቡ ሕንጻዎች | 3 | 89,162,355.00 | ›› |
| 5. | መድኃኒት ቤቶች | 3 | 3,114,460.00 | ›› |
| 6. | ካፌና ምግብ ቤቶች | 10 | 1,967,402.00 | ›› |
| 7. | ላውንደሪ | 1 | 207,354.00 | ›› |
| 8. | ድርጅቶች | 2 | 603,359.00 | ›› |
| 9. | ፎቶ ቤቶች | 2 | 5,809,648.00 | ›› |
| 10. | ተሽከርካሪዎች | 3 | 1,164,697.00 | ›› |
| | ድምር | 151 | 349,741,867.00 | |
| 11. | መኖሪያ ቤቶች | 1 | 30,000.00 | ንብረትነታቸው የእስልምና እምነት ተካታይ የሆኑ ሰዎች |
| 12. | የንግድ ተቋማት | 11 | 4,207,770.00 | ›› |
| | ድምር | 12 | 4,237,770 | |

በአጠቃላይ ጉዳቱ 163 ያህል ቤቶችና ንብረቶች ላይ የደረሰ ሲሆን፤ የጉዳት መጠኑ ድምርም 353,979,637 የሚገመት መሆኑን የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት በቁጥር ጠ/ም/0990/12/27/12 በ27/05/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ገልጾልናል፡፡

ይህ መግለጫ በሚወጣበት ወቅት ጉዳት የደረሰባቸው የግለሰቦች መኖሪያ ቤቶችና የንግድ ድርጅቶች በግምታቸው መሠረት የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ም/ቤት ካሰባሰበው የገቢ ማሰባሰቢያ ከተገኘ ገንዘብ የጠከፈላቸው መሆኑንና የመስጊዶች ጥገና ግን እየተሰራ እንዳልሆነ ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

በኃይማኖት ሰበብ የሚፈጠሩ ግጭቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እከፉና እየተባባሱ በእምነት ተቋማትና ተከታዮቻቸው ላይ እየተፈጸመ ያለው ውድመትና የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ሊወገዝ ይገባዋል፡፡ ኃይማኖትን መነሻ በማድረግ የተፈጠሩ ግጭቶችን ለመከላከልና ለማስወገድ መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በጥፋቱ የተሳተፉትን አክራሪዎችና ተባባሪዎቻቸውን ለፍርድ እንዲቀርቡ እያሳሰብን፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነት ችግር እንዳይፈጠር መንግሥት አስፈላጊውን ከለላ እና ጥበቃ እንዲያደርግ ኢሰመጉ ያሳስባል፡፡

## ክፍል ሁለት

## 5. ማሳሰቢያ

በዚህ መግለጫ ውስጥ በተካተቱ የምርመራ ግኝቶች ላይ በመመሥረት ኢሰመጉ ለሚከተሉት አካላት ማሳሰቢያውን እንደሚከተለው ያቀርባል፡፡

**የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶቹ የተፈጸሙባቸውን አካባቢዎች የሚያስተዳድሩ የክልል መስተዳድሮችና የፌዴራል መንግሥት**

- የተለያዩ ብሔሮች ተወላጆች በጋራ በሚኖሩባቸው ክልሎችና በተዋሳኝ ክልሎች መካከል ለሚነሡ ግጭቶች መንሥዔ የሚሆኑ ሁኔታዎችን እንዲያሻሽሉ፤
- በብሔር ተኮር ግጭቶችና ጥቃቶች ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ቀዬአቸው ተመልሰው ሰላማዊ ኑሮ መምራት የሚችሉበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ፤
- የዜጎችን በመረጡት የሐገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመሥረት ነጻነት እንዲያከብሩ፣ እንዲያስከብሩና ይህም የሚፈጸምበትን ሁኔታ እንዲያሟሉ፤
- የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶቹ የተፈጸሙባቸውን አካባቢዎች የሚያስተዳድሩ የክልል መስተዳድሮችና የፌዴራል መንግሥት በዚህ መግለጫ የተካተቱትን የሰብዓዊ መብቶችን የጣሱ አካላት ሁሉ በሕግ እንዲጠየቁ እንዲያደርጉ፣ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነት ችግሮች እንዳይከሰቱ የመከላከልና ለዜጎች ጥበቃ የማድረግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ፤
- ከብሔር ተኮር ፖሊቲካዊ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በየአካባቢው የተለያየ ሥያሜ በመያዝ የሚፈጠሩ የወጣቶች መሰባሰቢያ ቡድኖች ለቁጥጥር በሚያመች መልኩ ሕጋዊ ሰውነት ኖሯቸው እንዲቋቋሙ በማድረግ ሥርዓት አልበኛነት እንዳይሰፍን እንዲከላከሉ፤
- በዜጎች ላይ የሕይወት፣ የአካልና የንብረት ጉዳት ያደረሱና ጉዳቱ እንዲደርስ ያደረጉ ግለሰቦች፣ በዜጎች ላይ ጉዳት ሲደርስ በቸልታ የተመለከቱና ኃላፊነታቸውን ያልተወጡ የመንግስት ኃላፊዎች ለሕግ እንዲቀርቡ፤
- ከመንግሥት መዋቅር ውጭ የሆኑ ታጣቂ ኃይሎችን ትጥቅ በማስፈታት ወደ ማኅበረሰቡ ተቀላቅለው ሰላማዊ ሕይወት መጀመር የሚችሉበትን መንገድ እንዲያመቻቹ፤
- በዚህ መግለጫ የተጠቀሱ ብሔር ተኮር ጥቃቶችና ግጭቶችን መነሻ ምክንያት መንግሥት ጥናት በማድረግ፣ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች መባባስ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ሕጎች፣ ፖሊሲዎችና አሠራሮች ላይ የእርምት እርምጃ እንዲወስድና ዘለቄታዊ መፍትሔ እንዲሰጡ፤
- በሀገራችን የሚገኙ ብሔራዊ የሰብዓዊ መብቶች ተቋማትን የእስከዛሬ የሥራ እንቅስቃሴያቸውን በመገምገም የተጣለባቸው ተቋማዊ የሰብዓዊ መብቶችን የማስከበር ግዴታቸውን በብቃትና በገለልተኝነት የሚሰሩበትን ሁኔታ እንዲያመቻቹ፤
- ለሟች ቤተሰቦችና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ግለሰቦች ተገቢው የሞራል እና የገንዘብ ካሣ እንዲከፈል፣ ቤታቸው የፈረሰባቸው ዜጎች ተገቢውን ካሳ እንዲያገኙ እንዲደረግ ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

**ብሔራዊ የሰብዓዊ መብቶች ተከላካይ ተቋማት (የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የፍትሕ አካላት)**

- ለሕግ የበላይነትና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩላቸውን ጥረት በማድረግ በተቋቋሙበት ሕግ እና በፓሪስ ስምምነት መርሖዎች የተጣለባቸውን ግዴታ እንዲወጡ፤
- ከኢሰመጉና በሕጋዊ መንገድ ከሚንቀሳቀሱ ሌሎች መሰል የመብት ተከላካይ ተቋማት ጋር በቅርበት ተባብሮ በመሥራት በኢትዮጵያ ያለው የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ ይሻሻል ዘንድ በመንግሥት ላይ ጫና እንዲያሳድሩ፤

**የ.ተ.መ.ድ የሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ**

- በኢትዮጵያ ያለውን የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በመከታተል ከዚህ በኋላ ተመሳሳይ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዳይፈጸሙ ለመከላከል የሚረዱ እርምጃዎችን እንዲወስድና የ.ተ.መ.ድ ጠቅላላ ጉባዔም ተመሳሳይ እርምጃ ይወስድ ዘንድ ግፊት እንዲያደርግ፤
- ኢትዮጵያ አጽድቃ የሐገሪቱ ሕግ አካል ያደረገቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በማክበር ያለባትን ግዴታ ትወጣ ዘንድ ጥሪ እንዲያቀርብ ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡

## 6. ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች በተለያዩ ጊዜያት ብሔር ተኮር የሆኑ ጥቃቶችና ግጭቶች በተለያዩ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ሲቀሰቀሱና የበርካታ ወገኖች ሕይወትና ንብረት ሲጠፋ፣ አካል ሲጐድል፣ እንዲሁም ሰላማዊ ዜጐች ከመኖሪያቸው ሲፈናቀሉ እንደነበር ይህም ጉዳይ በቂ ትኩረት፣ ዘለቄታዊና ሕጋዊ መፍትሄ በአስቸኳይ እንዲሰጠው በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው የተለያዩ መግለጫዎቹ ከክልል እስከ ፌደራል እርከን ለሚገኙ የመንግስት አካላት ሲያሳውቅና ሲያሳስብ መቆየቱ ይታወቃል።

በሀገራችን ብሔር ተኮር ለሆኑ ጥቃቶችና ግጭቶች በቂ ትኩረት አልተሰጣቸውም። ለግጭቶቹ መነሻ የሆኑ ችግሮችን ኅብረተሰቡ በተለያዩ መንገዶች ለመንግሥት ሲያስተላልፍ ቢቆይም ለሚያቀርባቸው ጥያቄዎችና ቅሬታዎች በመንግስት በኩል በእውነተኛነት በማዳመጥ ለግጭቶቹ መቀስቀስ ምክንያት የሆኑትን መነሻ ችግሮች በማጥናት፣ ፖለቲካዊና ሕጋዊ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ በጥቃቶቹና በግጭቶቹ ውስጥ እጃቸው ያለበት አካላትን ተጠያቂ በማድረግ፣ ዜጎችን በሀገራቸው በእኩልነትና በሰላም በፈለጉት ቦታ የፈለጉትን ሥራ ሠርተው የመኖር ሕገ መንግሥታዊ መብቶቻቸው ተከብሮ እንዲኖሩ በማረጋገጥ በኩል መንግሥት ተገቢውን ጥረት እያደረገ ነው ለማለት አያስደፍርም።

በዚህ ረገድ መንግስት ችግሮች ከመከሰታቸውና የሰው ሕይወት ጠፍቶ የአካል ጉዳትና ንብረት ውድመት ከማስከተላቸው በፊት በቂና አስተማማኝ፣ ተቋማዊና ዘላቂ የሆነ ለዜጎች ዋስትና የሚሰጥ እርምጃ መወሰድ ላይ ገና ብዙ ይቀረዋል። ችግሮቹ ከተፈፀሙም በኋላ ተጠያቂነትን የማስፈን፣ የዜጐችን የህይወትና የአካል ደህንነት የመጠበቅ፣ ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ ኑሮን የመመስረት ሕገ መንግስታዊ መብት በማረጋገጥ ረገድ በመንግስት በኩል ከፍተኛ ድክመት ይታያል።

በአገራችን በተለያዩ አከባቢዎች ዜጎች በብሔር ማንነታቸው ብቻ ጥቃቶች እየተፈጸመባቸው የብዙ ወገኖች ሕይወት አልፏል፣ የአካል ጉዳት ደርሷል፣ ሚሊዮኖች ከቀያቸው ተፈናቅለዋል፣ በርካታ ንብረት ወድሟል። ማንም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በፈለገበት የሀገሪቱ ክፍል ተዘዋውሮ ኑሮውን የመመስረት እና ሰርቶ የመኖር ሕገ መንግሥታዊ መብት አለው። ከዚህ በተቃራኒ በማን አለብኝነት የዜጎች ሰብዓዊ መብቶች በተደራጁና በታጠቁ ኃይሎች እየተጣሰ ቢገኝም መንግሥት እነዚህን ሰብዓዊ ጥሰቶች ማስቆምና የዜጎችን ሰላምና ደኅንነት ከማስጠበቅ ይልቅ ችግሮች ከተከሰቱ በኋላ እሳት ማጥፋት ላይ የተጠመደ ይመስላል።

ብሔር ተኮር ጥቃቶችና ግጭቶች ላይ እጃቸውን ያስገቡና ዋና ተዋናዮች ለሕግ ባለመቅረባቸውና ተመጣጣኝ የሆነ አስተማሪና ሕጋዊ እርምጃ መንግስት ባለመውሰዱ ነገሩ ከቀን ወደ ቀን እየሰፋ ሄዶ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ሰላምና መረጋጋት ብሎም ደህነነት ላይ ከፍተኛ ስጋት እየፈጠረ ይገኛል።

በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በህዝብ የሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎች በተለይም የህግ የበላይነት የማረጋገጥ ጥያቄዎች፣ የዴሞክራሲ ጥያቄዎችን የመልካም አስተዳደር ቅሬታዎች፣ የሰብዓዊ መብቶችንና የተለያዩ ጥያቄዎችን በወቅቱ በዴሞክራሲያዊና በሕጋዊ መንገድ ከህዝብ ጋር በመነጋገር ዘለቄታዊ መፍትሄ መንግስት መፈለግ እንደሚኖርበት ኢሰመጉ ያምናል።

በአንድ ሀገር ውስጥ ብቸኛው የኃይል ባለቤት (Monopoly of Power) መሆን የሚገባው መንግስት ብቻ መሆኑን ኢሰመጉ ያምናል። ከእዚህ አንጻር በተለያዩ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ የሚገኙ

ታጣቂ ኃይሎች በንፁሐን ዜጎች ላይ እየፈፀሙት ያሉት ግድያና መጠነ ሰፊ ጥፋት በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት አስቸኳይ ትኩረትና ሕጋዊ መፍትሄ እንዲሰጠው ኢሰመጉ በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው የተለያዩ መግለጫዎቹ ከክልል እስከ ፌዴራል እርከን ለሚገኙ የመንግስት አካላት ሲያሳስብ መቆየቱ ይታወቃል፡፡

ሕይወት መጥፋት፣ መቁሰልና ለከፍተኛ የንብረት መውደም ብሎም ለሀገሪቱ አለመረጋጋት ምክንያት ሆነዋል፡፡ የሚመለከታቸው የክልልም ሆነ የፌዴራል የመንግስት ተቋማት ይህንን ከባድ ችግር በቂ ትኩረት በመስጠት ሕጋዊና አስተማማኝ ሥራ መስራትና የዜጎችን በሰላም የመኖር፣ ወጥቶ የመግባትና ንብረት የማፍራት መብቶቻቸው ላይ የተጋረጠውን ከፍተኛ አደጋ መፍትሄ ሊሰጠው እንደሚገባ ኢሰመጉ ያምናል፡፡

እነዚህ የታጠቁ ኃይሎች በተለያዩ አካባቢዎች ተደራጅተው በመሳሪያ የተደገፈ ዝርፊያ፣ በውጭ ሀገር ባለሀብቶች ላይ ጭምር ግድያ ሲፈፅሙ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ይሁንና እስከ አሁን ድረስ መንግሥት በዚህ ረገድ ጠንከር ያለ ሕግ የማስከበር ስራ ሲሰራ አልታየም፡፡ በመሆኑም መንግስት የሕግ የበላይነትን በቁርጠኝነት እንዲያስከብር ኢሰመጉ አሁንም በዚህ 38ኛ መደበኛ መግለጫው አበክሮ ያሳስባል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) ብሔርን መሰረት ያደረጉ ጥቃቶችና ግጭቶች በቂ ትኩረት፣ የማያዳግም፣ ዘለቄታዊ ፖለቲካዊና ሕጋዊ መፍትሄ እንዲሰጣቸው በተደጋጋሚ በሚያወጣቸው የተለያዩ መግለጫዎቹ ከክልል እስከ ፌደራል እርከን ለሚገኙ የመንግስት አካላት በተደጋጋሚ ሲጠይቅና ሲያሳስብ መቆየቱ ይታወቃል። ብሔርን መሰረት ያደረጉ ግጭቶች በሀገር ላይ እያስከተሉ ያሉት ዘርፈ ብዙ ውድመት ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ በተደጋጋሚ ታይቷል። ለወደፊት መሰል ግጭቶች እንዳይከሰቱ ከፌዴራል እስከ ክልል ያሉ የመንግስት መዋቅሮች እና ባለስልጣናትም ሆኑ የተፎካካሪ የፖለቲካ ቡድኖች ራሳቸውን እንዲመለከቱ፣ ህዝብን ከህዝብ ከሚያጋጭና ሀገርን ከሚጎዳ ድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ኢሰመጉ አጥብቆ ይጠይቃል፡፡

ለጥቃቶቹና ግጭቶቹ መፈፀም ምክንያት የሆኑትን መነሻ ችግሮች በማጥናት፣ ሕጋዊና ፖለቲካዊ እርምጃዎችን በመውሰድ በሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ላይ እጃቸው ያለበት አካላትን ተጠያቂ በማድረግ፣ ዜጎችን በሀገራቸው በእኩልነትና በሰላም የሚኖሩበትን ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲያመቻቹ ኢሰመጉ በድጋሚ በዚህ 38ኛ መደበኛ መግለጫው ጥሪውን ያቀርባል፡፡

በመጨረሻም፣ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የቆማችሁ ዜጎች፣ ሐገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማትም መንግሥት የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲያከብር፣ እንዲያስከብርና እንዲያሟላ ከዚህ በታች በተገለጹት አድራሻዎች በመጻፍና ስልክ በመደወል ጥያቄና ግፊት እንድታደርጉ ኢሰመጉ ይጠይቃል፡፡ **በተለይም፡-**

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት**

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 80001፣ኢ-ሜል፡- national.parliament@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 155-0400፣ የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 124-1000፣
  አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪፌደሬሽንምክርቤትአፈ-ጉባዔጽ/ቤት:-**

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 20122/1000፣ኢ-ሜል፡- kumashih@gmail.com
  ፋክስ፡- (+251) 011 124-1208/011 124-2308፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 122-3322፣
አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 23698፣ ፋክስ፡- (+251) 011 551- 8656፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 551-8186፣
  አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት :-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡-1031፣ ፋክስ፡- (+251) 011 122-6292፣
  የስልክቁጥር፡- (+251) 011 124-1155፣
  አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ
- **የፌዴራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ**
  ስልክ ቁጥር +251 115541868
  ፋክስ +25115517775
  ኢሜይል MOJMO@ETHIONET.ET
  አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 5608፣ ኢ-ሜል፡- mofatr1@yahoo.com፣
  ፋክስ፡-(+251)011 551-1200፣
  የስልክ ቁጥር፡-(+251) 011 515-3204፣
  አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 2459፣ኢ-ሜል:ombudsmaneth@ethionet.et፣
  ፋክስ፡- (+251) 011 553-2073፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 543-336፣
  አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ
- **ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን:**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1165፣ኢ-ሜ: hrcom@ethionet.et፣
  ፋክስ: (+251) 011 550-4125፣
  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 550-4031፣
  አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ
- **ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌደራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጀነራል ጽ/ቤት:**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 199፣ የስልክቁጥር፡- (+251) 011 551-2744፣
  አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ
- **ለሶማሌ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:**
  ፖ.ሳ.ቁጥር 392፣ ፋክስ፡- (+251) 25 775-3429፣
  የስልክ ቁጥር: (+251) 257 75 34 29
  ጅግጅጋ፣ኢትዮጵያ
- **ለሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-**
  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 588 ፋክስ፡- (+251) 025 775-2325፣
  የስልክቁጥር፡- (+251) 025 775-4038 / 025 775-3241

ጂግጂጋ፣ኢትዮጵያ

- **ለኦሮሚያ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769፣ኢ-ሜል፡- oromiawiev@ethionet.et፣

ፋክስ፡- (+251) 011 551-3642 / (+251) 011 551-9633፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 552-4247፣

አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ

- **ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 101769 ፋክስ፡- (+251) 011 552-4247

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 011 555-0455

አዲስአበባ፣ኢትዮጵያ

- **ለአማራ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1324፣ ፋክስ፡- (+251) 058 220-2511፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-2659፣

ባሕር ዳር፣ኢትዮጵያ

- **ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 312 ፋክስ፡- (+251) 058 220-1068፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 058 220-0924 / 058 220-0499

ባህር ዳር፣ኢትዮጵያ

- **ለደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 1546፣ ፋክስ፡- (+251) 046 220-2408፣

የስልክቁጥር፡- (+251) 046 221-4778/ 046 220-5848፣

ሐዋሳ፣ኢትዮጵያ

- **ለደ/ብ/ብ/ህ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 18 ፋክስ፡- (+251) 046 220-1641፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 046 220-9166

ሐዋሳ፣ኢትዮጵያ

- **ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ም/ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 44፣ ፋክስ፡- (+251) 057 775-0814፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 055 7775-0109፣

አሶሳ፣ኢትዮጵያ

- **ለትግራይ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 291፣ ፋክስ፡- (+251) 034 441-6564፣

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 034 441-6563፣

መቀሌ፣ኢትዮጵያ

- **ለጋምቤላ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 25፣ፋክስ:- (+251) 046 220-2408፣

ጋምቤላ፣ኢትዮጵያ

- **ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 025

የስልክ ቁጥር፡- (+251) 047 551-1544

ጋምቤላ፣ኢትዮጵያ

- **ለሐረሪ ክልል ምክር ቤት አፈ-ጉባዔ ጽ/ቤት:-**

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 952 ፋክስ፡- (+251) 025 666-2530፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1723 / 025 666-1746

  ሐረር፣ኢትዮጵያ

- **ለሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት:-**

  ፖ.ሳ.ቁጥር፡- 272 ፋክስ፡- (+251) 025 666-0666፣

  የስልክ ቁጥር፡- (+251) 025 666-1799

  ሐረር፣ኢትዮጵያ

- **ለአፋር ክልል ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት**

  ስልክ ቁጥር (+251) 0336660056

  ሰመራ፣ኢትዮጵያ

- **ለድሬዳዋ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት**

  የስልክ ቁጥር፡ (+251) 025 11 11 358

  ፋክስ፡ (+251) 025 11 19 805

- **ለአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የከንቲባ ጽ/ቤት**

  ስልክ ቁጥር (+251) 0118591363

ኢ.ሰመጉ የቆመው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መዳበር፣ ለሕግ የበላይነት መስፈንና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ነው!!

ኢ.ሰመጉ በአፍሪካ የሕዝቦችና የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን የታዛቢነት ቦታ አለው፤
የዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ፌዴሬሽ (FIDH) አባል፣
የዓለም ዓቀፍ ፀረ-ስቃይ ድርጅት (OMCT) አባል፣
የምሥራቅና የአፍሪካ ቀንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ሕብረት (DefendDefenders)
መሥራች አባልም ነው፡፡